# የኢፌዲሪ ሕገ-መንግስትና
# የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ሕዝቦች
# ታሪክናተጠቃሚነት

## ለ9ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና
## ሕዝቦች ቀን በዓል ለውይይት የቀረበ

ህዳር 2007 ዓ.ም

<u>አሶሳ</u>፤

ማውጫ

መግቢያ ....................................................................................... 1

ክፍል አንድ፡- የክልሉ ነባር ብሄረሰቦች ጥንተ- ታሪክ፣ ምንጭ ስያሜና አሰፋፈር

1.1 የበርታ ብሔረሰብ ጥንተ- ታሪክና ምንጭ ...................................... 2

1.2 የጉምዝ ብሄረሰብ ጥንተ- ታሪክና ምንጭ ...................................... 5

1.3 የቦሮ ሺናሻ ብሄረሰብ ጥንተ- ታሪክና ምንጭ ................................ 8

1.4 የማኦ ብሄረሰብ ጥንተ- ታሪክና ምንጭ ........................................ 11

1.5 የኮሞ ብሄረሰብ ጥንተ- ታሪክና ምንጭ ........................................ 14

ክፍል ሁለት፡- የክልሉ አጠቃላይ ገፅታ........................................................ 15

2.1 ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥና የተፈጥሮ ሀብት.................................. 15
2.2 አስተዳደራዊ ገፅታ.......................................................................... 17

ክፍል ሶስት፡- ባለፉት ሥርዓቶች የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ህዝቦች ይደርስባቸው የነበረ ጭቆናና ያካሄዱት ትግል........................................................ 17

ክፍል አራት፡- በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የተገኙ ውጤቶችና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ህዝቦች ተጠቃሚነት........................................................ 19

4.1 በፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ የመንግስት አወቃቀርና በዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የተገኙ ውጤቶች ........................................................................ 19

4.2 የክልሉ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ............................ 19

4.3 በፖለቲካ ዘርፍ የተገኙ ውጤቶችና የክልሉ ህዝቦች ተጠቃሚነት............ 21

4.4 ቀልጣፋና ተደራሽነት ያለው የፍትህ ሥርዓት በመዘርጋት በኩል የተገኙ ውጤቶች.................................................................................... 22

4.5 በመልካም አስተዳደር የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ህዝቦች ተጠቃሚነት............. 26

ክፍል አምስት፡- በኢኮኖሚ ዘርፍ የተገኙ ውጤቶችና ለውጦች.............................. 27

5.1 የግብርናና ገጠር ልማት ............................................................ 27

5.2 ኢንቨስትመንት.............................................................................. 29

5.3 ገቢ አሰባሰብ................................................................................ 30

5.4 የመንደር ማሰባሰብ ሥራዎች......................................................... 31

5.5 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ..................................... 31

ክፍል ስድስት፡- በመሠረተ ልማት ዘርፍ የተገኙ ውጤቶችና ለውጦች........................ 33

6.1 መንገድ ........................................................................................ 33

6.2 ቴሌኮሙኒኬሽን .............................................................................. 34

6.3 የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት.......................................................... 34

6.4 ባንክ ............................................................................................ 35

6.5 ብድርና ቁጠባ ተቋም .......................................................................... 35

6.6 መብራት ........................................................................................ 35

ክፍል ሰባት፡- በማህበራዊ ዘርፍ የተገኙ ውጤቶችና ለውጦች.............................. 36

7.1 ትምህርት ..................................................................................... 36

7.2 ጤና .............................................................................................. 39

ክፍል ስምንት፡- የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች................................................. 41

ማጣቀሻዎች ......................................................................................... 44


## መግቢያ

አገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መኖሪያ፤ ለዘመናት ነፃነቷን አስጠብቃ የኖረችና የረጅም ዘመን ታሪክ ባለቤት ስትሆን በመቻቻል፣ በመፈቃቀርና አብሮ በመኖር ባህል ለዓለም በምሣሌነት የምትጠቀስ ሀገር ናት፡፡ ሆኖም ግን ለረጅም ዘመናት በሀገሪቱ ሰፍነው በቆዩ መንግስታትና የፖለቲካ ስርዓቶች ነገስታቶቿ ስልጣናቸውን ተጠያቂነት በሌለው መልኩ አገሪቱን በፈለጉትና በመሰላቸው መንገድ ሲገዙ መቆየታቸው የሚታወስ ነው፡፡ ነገስታቱ ከተለየ የዘር ሀረግ እንደተገኙና ለመግዛትም በፈጣሪ እንደተቀቡ በማስመሰል ሀይማኖትን በመሳሪያነት ተጠቅመው ህዝቡ የነገስታቱን አገዛዝ ያለማንገራገር እንዲቀበል ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ የፖለቲካ ስርዓቱንና የአገዛዝ ዘመናቸውን ለማራዘምም የኢትዮጵያ ህዝቦችን ብዙህነት ወደ ጎን በመተው ሀገሪቱ ፈጣሪ በመረጠው በአንድ ብቸኛ መሪ የምትመራ፤ የአንድ ህዝብ፤ የአንድ ባህል፤ የአንድ ቋንቋ እና የአንድ ሃይማኖት ሀገር እንደሆነች አስመስሎ በማቅረብ ለዘመናት ሲገዙ ቆይተዋል፡፡ በእነዚህ ዘውዳዊ

ስርዓቶች የተጻፉ የተወሰኑ ህገ-መንግስቶችና የፓርላማ ስርዓቶች ቢኖሩም ህገ መንግስቶቹም ሆኑ ፓርላማዎቹ ለይስሙላ የተዋቀሩና የነበረውን ዘውዳዊ አገዛዝ ከማጠናከርና ከማጎልበት ባሻገር ስልጣንን ለህዝብ በማውረድ ረገድ ፋይዳ አልነበራቸውም፡፡

የዘውዳዊ ስርዓት ከተወገደ በኋላም በብዙ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ ሀገሪቱ ሰላማዊ የመንግስት ሽግግር በማድረግ የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባት ሀገር ትሆናለች የሚል እምነትና ተስፋ የነበረ ቢሆንም ስልጣን የህዝብ መሆኑ ቀርቶ ወታደራዊ ደርግ ጊዜያዊ  መንግስት በሚል ሽፋን ስልጣን ላይ በመውጣት ከዚያም ወደ የለየለት አሃዳዊና አምባገነናዊ  መንግሥት በመለወጡ የብሄራዊ ኩራታችን ምንጭ የሆነውን ብዝሃነት ፍፁም ማስተናገድ ወደማይችልበት ደረጃ ተሸጋግሮ ነበር፡፡በመሆኑም እስከ ደርግ ሥርዓት ውድቀት በነበረው የአገዛዝ ዘመን የአገራችን ህዝቦች በብሄርና በመደብ ጭቆና ሥር ወድቀው ለዘመናት ሲጨቆኑ ቆይቷል፡፡

እነዚህ የጭቆናና የአፈና ስርዓቶች በፈጠሩትና ለበርካታ ዓመታት በተከማቹ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች እንዲሁም የብሄር ብሔረሰቦች የማንነት ጥያቄዎች የፈጠሩትን ጫና ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ባካሄዱት ትግል በአገሪቱ አዲስ የፖለቲካ ስርዓት ተቋቁሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በመከሩበትና በተስማሙት ሁኔታ የፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ህገ መንግስት ተመስርቶ ብሔሮችና ብሔረሰቦች የማንነት ጥያቄያቸው ምላሽ አግኝቶ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ተከብሮላቸዋል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበና የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነት ላይ የተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ለመፍጠር በሕዝቦቹ ሙሉ ፍቃድና ይሁንታ የፀደቀው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓትና ዴሞክራሲዊ አንድነት እውን ሆኗል፡፡

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህዝቦችም እንደሌሎች የሀገሪቱ ብሄሮች፤ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሁሉ በተደራጀም ሆነ ባልተደራጀ መልኩ በተለያዩ ጊዜያት ከትግሉ ጎራ በመሰለፍ በላያቸው ላይ ተጭኖ የነበረውን የጭቆና ቀንበር ከሥር መሠረቱ አሽቀንጥረው ለመጣል በቅተዋል፡፡ የክልሉ ህዝቦች ማንነታቸው፣ ባህላቸውና ታሪካቸው እንዲሁም የራስን እድል በራስ የመወሰን መብታቸው በህገ መንግስቱ የተረጋገጠ ከመሆኑ ባሻገር የህገ መንግስቱ ቱርፋት የሆኑ በርካታ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጦችና ውጤቶች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ በፍላጎትና በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ከመፍጠር አኳያ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሕዝቦች ባለፉት 23 ዓመታት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ዘርፎች እንዲሁም በመልካም አስተዳደር፣ በፍትህና በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ያስመዘገቧቸው ድሎችና የተገኙ ለውጦችን መዳሰስና የሕዝቡን ተጠቃሚነት ማሳየት ው፡፡

የጥናታዊ ጽሑፍ አደረጃጀትም መግቢያን ጨምሮ ስምንት ክፍሎች ያሉት ሲሆን መግቢያው የጽሁፍን ጠቅላላ ሁኔታ እና ዓላማዎች ጠቅለል ባለመለኩ ያቀርባል፡፡ ክፍል አንድ የክልሉ ነባር ብሄረሰቦች ጥንተ ታሪክ፣ ምንጭ፣ ስያሜና አሰፋፈር ይተነትናል፡፡ ክፍል ሁለት የክልሉ አጠቃላይ ገፅታ ይዳስሳል፣ ክፍል ሦስት ባለፉት ሥርዓቶች የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ህዝቦች ሲደርስባቸው የነበሩ ጭቆናዎች፤ ያካሄዱት ትግልና የተገኙ ውጤቶችን ይተነትናል፣ ክፍል አራት በፍትህና መልካም አስተዳደር ዘርፍ የተመዘገቡ ውጤቶችና የክልሉ ህዝብ ተጠቃሚነት፣ ክፍል አምስት በኢኮኖሚ ዘርፍ የተገኙ ውጤቶችና ለውጦች፣ ክፍል ስድስት በመሠረተ-ልማት ዘርፍ የተገኙ ውጤቶችና ለውጦች፣ ክፍል ሰባት በማህበራዊ ዘርፍ የተገኙ ውጤቶችና ለውጦች የሚዳስስ ሲሆን ክፍል ስምንት የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች የያዘ ነው፡፡

### ክፍል አንድ፡ የክልሉ ነባር ብሄረሰቦች ጥንተ ታሪክ፣ ምንጭ፣ ስያሜና አሰፋፈር

### 1.1 የበርታ ብሔረሰብ ጥንተ-ታሪክና ምንጭ

የህዝቦችን ታሪክ በአግባቡ በማጥናትና በመመዝገብ ማንነታቸውንና የታሪክ ምንጫቸውን ማወቅና ማሳወቅ ጠቀሜታው የጎላ ከመሆኑም በተጨማሪ ለቀጣይ ትውልድ ታሪክን በማውረስ ትውልድ በመፈቃቀርና በመዋደድ አብሮ እንዲኖር በማድረግ ሰፊ ድርሻ አለው፡፡

ዛሬ በሀገራችን የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦቾ ባህል፣ ቋንቋና ታሪክ ተጠብቆና ዳብሮ እንዲቆይ፣ እንዲሁም በፅሁፍና በሌላም መንገድ ለትውልድ እንዲተላለፍ ይበረታታል፡፡

በሌላ በኩል እንደማንኛውም ህዝብ የበረታ ህዝብም የራሳቸው የሆነ ታሪካዊ አመጣጥና ምንጭ እንዲሁም አሰፋፈር፣ ባህል፣ ቋንቋና ታሪክ ያላቸው መሆኑ ታሪካቸው በሚገባ መታወቅ ያለበት ያደርገዋል፡፡

የረጅም ጊዜ ታሪክና ባህል ባለቤት የሆነዉ ይኸዉ ብሄረሰብ ብዙ ሺ ዓመታት የቆየ ናይሎቲክ ጥንታዊ የአፍሪካ ብሄረሰብ ነዉ፡፡ ብሔረሰቡ በምስራቃዊ ስናር /ሱዳን/ ግዛት የየገሪን የሚባለውን ተራራማ ቦታ ሰፊ ግዛትና በኢትዮጵያ ውስጥ የአባይንና የዳቡስ ሸለቋማ አካባቢን ይዞ ለረጅም ጊዜ የኖረ ህዝብ ነው፡፡

ከጥንታዊ ግብፃዊያን ጋር ግንኙነት እንደነበረዉ በግብፅ ፈርኦኖችና ፒራሚዶች ላይ የቤላሻንጉል የወርቅ ቁፋሮ የያዙ ፅሁፎች ይገኛሉ፡፡ ከጥንታዊ አክሱማዊያን ጋር ጠንካራ የንግድ ግንኙነት እንደነበሯቸው በንጉስ ኢዛና ገድል ዉስጥ የሳሱ ምድር ወርቅ ጉዳይ መስፈር የተጠቀሰዉ ህዝቡ ከጥንት ጀምሮ የኑሮ መሰረት እንደነበረ ያሳያል፡፡ ለግብፅ ፈርኦኖች፣ ለአክሱምና ለመረዌ ነገስታት የሰው ኃይል እና የወርቅ ንግድ ምንጭ በመሆን ግንኙነት እንደ ነበረው የታሪክ መዛግብት ይገልጻሉ፡፡ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት አሁንም ቢሆን ክልሉ የወርቅ ሀብት ክምችት እንዳለው የሚያሳዩ ሁኔታዎች አሉ፡፡

ዛሬም ይህ የደለል ወርቅ ማበጠርና ማንጠር የብሄረሰቡ ቀዳሚ ተግባር ቢሆንም ብሄረሰቡ ለረጅም ዘመናት በከብት እርባታ፣ በንብ ማነብ፣ በንግድ እንዲሁም በእርሻ ስራ ይተዳደሩ ነበር፡፡ ከዚህ በመነሳት እንደሚነገርለት ከሆነ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋስትናዉ የቤላሻንጉል ወርቅ ነበር፡፡

ሱዳንና ኢትዮጵያ የሚል ስም ከመዉጣቱ በፊት በርታዎች ከቢርቢር እስከ ስናር ሰፊ ግዛት ይዞ የኖሩ ቀደምት የናይሎቲክ የአፍሪካ ብሄረሰብ ነበረ፡፡ ከ1902 ዓ.ም በፊት በኢትዮጵያ እና በሱዳን ቅኝ ገዥዎች የድንበር ከለላ ሳይደረግ ይህ የኢትዬጵያ በርታ ነዉ ይኸኛዉ ደግሞ የሱዳን በርታ ነዉ የሚል መጠሪያ አልነበረም፡፡ ይህም የራሳቸዉ ሰፊ ግዛት ይዞ የኖሩ መሆኑን ያሳያል፡፡

በ1902 ዓ.ም በአፄ ምኒልክ እና የሱዳን ቅኝ ገዥዎች በተደረገዉ የድንበር ከለላ መሰረት ድንበሩ በርታዎችን በሁለት በመክፈል ከድንበር እስከ ስናር ያለዉ የሱዳን በርታ ሲባል ከድንበር እስከ ቤጊ፣ መንዲ፣ ግዳሜና ሌሎች ቦታዎች ያሉት የኢትዮጵያ በርታ ተባሉ፡፡ በብሄረሰቡ አገላለጽ ሕዝቡ ወደ ሱዳን መስፋፋት የጀመሩት ከኢትዮጵያ መነሻ በማድርግ እንደነበረ ይገልፃሉ፡፡ ይህን አስመልክቶ የታሪክ ፀሐፊዎችና አገር ጉብኝዎች ስለብሄረሰቡ ጥንታዊ ምንጭ ከመጠቃቀሳቸው በስተቀር ወጥ የሆነ የባህልና የታሪክ ጥናት አላደረጉም፡፡ ከዚህም ጋር አብሮ መንግስታት በተቀያየሩ ቁጥር የሚከሰተዉ የብሄረሰቡ መጠሪያ የስም መለዋወጥ ማለትም ጀበላዊ፣ ወጣዊጥ አሁንም ደግሞ በርታ ተብሎ ተሰየመ፡፡ ይህ የስም መለዋወጥ ብሔረሰቡም ሆነ ስለብሔረሰቡ ለማወቅ ለሚሹ ሁሉ

ሲያስቸግር ቆይቷል፡፡ በይበልጥም ስለብሄረሰቡ ለማወቅ የሚደረግ ጥረት ስለቤላሻንጉል አከባቢ ሁነኛ እዉቀት የሌላቸዉ አንዳንድ አጥኚዎችና በተለያዩ ጊዜያት የሚሰጡት መግለጫዎችና ቃለ-መጠይቆች ሁኔታዉን ይበልጥ እንደአወሳሰቡት መረዳት ይቻላል፡፡

## ስያሜና አሰፋፈር

በብሄረሰቡ እምነት የቤላሻንጉል በርታ የሚለው ስያሜ ያገኘዉ ከትክል ድንጋዮቹ እንደነበረ ይገልፃል፡፡ እነዚህ የትክል ድንጋዮች ዛሬ በሸርቆሌ ወረዳ በጌዛመተማ ቀበሌ የሚገኙ ሲሆን ከጥንት ጀምሮ የበርታ መሪዎች የቀብር ቦታ ሆኖ ሲያገለግል ነበረ፡፡ ድንጋዮችን ይዞት የመጣው ጀርገንዲ አልበህድ የተባሉ ግለሰብ ሲሆን ቦታዉን ተረክቦ ስያስተዳድር ነበር፡፡

ይህ በክብ ቅርጽ የተሰራ የቤላሻንጉል ታሪካዊ የትክል ድንጋይ ታሪካዊና የበርታ ህዝቦች መለያ ሆኖ ለረጅም አመታት እንደቆየ ይገመታል፡፡ ዛሬ የክልሉ መጠሪያ የሆነውና የበርታ ብሔረሰብን የሚወክለው "ቤኒሻንጉል" የሚለው አጠራር በመጀመሪያ የተከሰተው በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአረብ ነጋዴዎችና አስተማሪዎች ወደ አካባቢው ከመጡ በኋላ እንደነበረ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት ብሔረሰቡ ዛሬም "ቤላሻንጉል" ወይም "የትክል ድንጋይ" እያለ ራሱን ይጠራል፡፡

"ቤላ" ማለት ድንጋይ ማለት ነዉ ፡፡ "ሻንጉል" ደግሞ የንጉስ ስም ነዉ፡፡ ስለዚህ "ቤላሻንጉል" ማለት "የሻንጉል የንጉስ ድንጋይ" ማለት ነዉ፡፡ ይህ የትክል ድንጋይ የታላላቅ የብሄረሰቡ መሪዎች አፅምም ያረፈበት እንደነበረ ይገለፃል፡፡ አረቦች ወደዚህ አካባቢ ሲመጡ ቤላ የሚለዉን ወደ "ቤኒ" በመቀየር "ቤኒሻንጉል" አሉት፡፡ በአረበኛ "ቤኒ" የሚለው ቃላት የሚወክለው ልጆች ማለት ነዉ፡፡ ይህም የሻንጉል ልጆች በማለት እንደቀየሩት ይገመታል፡፡

በሌላ በኩል ስለብሄረሰቡ ለማወቅ የሚደረግ ጥረት ስለቤላሻንጉል ሁነኛ እዉቀት የሌላቸዉ አንዳንድ ፀሐፊዎችና የአገር ጉብኚዎች በተለያዩ ጊዜያት የሚሰጡት ገለፃዎች ብሄረሰቡ የዚህ አዱስ አካባቢ የሰፈሩት በ17ኛዉ ክፍለ ዘመን መጀመርያ አካባቢ እንደነበረ ብሄረሰቡ ወደ ኢትዮጵያ የመጡትም የስናሩ ፉይኝ ስርወ መንግስት ተከትለዉ እንዳልቀረ ይገልፃሉ፡፡ ነገር ግን በብሄረሰቡ ይህንን ሃሳብ ይቃወማሉ፡፡

በአጠቃላይ አሁንም ቢሆን የበርታ ህዝብ ዛሬ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት በአሶሳ ዞን በሚገኙ ቦታዎች ማለትም በአሶሳ፤ በባንባሲ፤ በሸርቆሌ፣ በኦዳ-ቡልዲግሉ፤ በማኦ-ኮሞ ልዩ ወረዳ፣በኩርሙክ፣በኮሞሻና በመንጌ እንዲሁም በካማሽ ዞን በስርባ-አባይና በቦሎጂጋንፎይ ወርዳዎችና በመተሃራ ዉስጥ ሰፍሮ የሚገኝ ሲሆን በሱዳን ግዛቶች ማለትም ደማሲን ፣ በሪሴሪስ ፣ በስንጃ ፣ በስናር ፣ በመደኒ እንዲሁም በካርቱም (ሱዳን) ሰፍሮ እንዳሉ ይታወቃል፡፡

ለብዙ ዘመናት የፉኝ ነገሥታት የቤላሻንጉል አካባቢ ተቆጣጥረዉ የግዛታቸዉ አካል ለማድረግ ብርቱ ጥረት ቢያደርጉም በበርታ ብሄረሰብ የረዥም ጊዜ ተጋድሎ ይህ ምኞታቸዉ ሳይሳካ መቆየቱን ታሪካዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ስለሆነም ፉኛዉያን ከሃይል ይልቅ የራስ ገዝ ሥርዓት ስልት የቤላሻንጉልን አካባቢ በሰላማዊ መልክ ለመቆጣጠር ሞክረዋል፡፡

ከ9ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን በንግድ ምክንያት ወደ ቤላሻንጉል ግዛት መግባት ጀመሩ፡፡ ይህን ተከትለው ከአገሬዉ ህዝብ ጋር የጋብቻ ትስስር መፍጠር ቻሉ፡፡ ፉኛዉያን የበርታ መሪዎችን በመጠጋትና የጋብቻ ትስስር በመፍጠር ለመሪዎቹ በረዳትነትና በአስተርጓሚነት በማገልገል በጊዜ

ሂደት የበርታን በትረ ሥልጣን እስከ መውረስ የደረሱ እንግዶች በመሆናቸዉ በ17ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን "ብልጦቹ እንግዶች" ተብሎ ተጠሩ፡፡

ስለዚህ ከብዙ ጊዜ የንግድና የጋብቻ ትስስር በኋላ የቤላሻንጉል መሪዎች በፉኝ ቅኝ ግዛት ተፅዕኖ ሥር መዉደቃቸዉ በተጨማሪ የበርታን ባህል ፣ ወግና ቋንቋ የተካኑ "መዩ" የሚባል አዲስ የበርታ ጎሣ መፍጠር ቻሉ፡፡ "መዩ" የሚለዉ ስም የተለያዩ ፍቺ ቢሰጠዉም በቤላሻንጉል ህዝብ የታወቀዉ "መዩ" ማለት ከበርታና ከፉኝ ጎሣ የሚወለድ "የአረብ ልጅ" ማለት ነዉ፡፡ ከ10ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን እስከ 17ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ በቤላሻንጉል  አካባቢ ሥልጣን ጨብጦ የቆዩ "መዮዎች" እንደነበሩ ይነገራል፡፡

በተለያዩ ዘዴዎች የገቡ እነኚህ ፉኛዊያን ግዛቲቱን የስናር መንግስት ትልቅ አካል ለማድረግ በቅተዋል፡፡ በ18ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን የቤላሻንጉል ታሪክ ለየት ያለ መልክ እንድኖር አድርጓል፡፡ የስናሩ በርታ በፉኝ ግዛት አማካኝነት ከአረቦች የእስልምና ሃይማኖት እንደተማሩ እና ከተቀበሉ ቆይተዋል፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ፉኛዊያን የእስልምና ባህል በቤላሻንጉል አካባቢ መስፋፋት ችለዋል፡፡ በዚህ ምክንያት በ17ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ በስናር መንግስት ላይ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ህዝባዊ አመፅ ተቀጣጥሎ እንደነበረ ይታወቃል፡፡

ይህ የተቀጣጠለዉ ብጥብጥ ወደ ቤላሻንጉል የህዝብ ፍልሰትን አስከትለዋል፡፡ ይህ የህዝብ ፍልሰት በታሪክ ዉስጥ "ሌ-ባላታ ሰዒድ" ፍልሰት ተብሎ ይታወቃል፡፡ በአረበኛ "አሰዒድ" ማለት ምስራቅ ማለት ስሆን አሁንም ከሱዳን በስተምስራቅ የሚገኙ ቤላሻንጉል "አዉላዳ ሰዒት" ተብሎ ይጠራሉ፡፡ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረዉ አረቦች ወደ እነዚህ አከባቢ መምጣት ከጀመሩ በኋላ ትምህርት ቤቶችን "መድረሳ" በማቋቋም የበርታ ልጆችን በማስተማር ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫዉተዋል፡፡ ከዚህም እጅግ ፈጣን የሆነ የጋብቻ ትስስር በማድረግ  ከሃገሩ ህዝብ ጋር ተቀላቅለዋል፡፡

በሌላ አገላለፅ አረቦች በነበራቸዉ የዕዉቀት፣የሃይማኖትና የንግድ ችሎታ ወደ ባላባቶች በመቅረብ የሥልጣን ተልዕኮም ትልማቸዉን ለማስፋት በቅተዋል፡፡ አረቦች በብዛት ሲመጡ የፉኝ መንግስት ማሽቆልቆል የጀመረበት ዘመን በመሆኑ በአካባቢው በበርታ ህዝብ ላይ የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅኖ ለማሳደር ችሏል፡፡ በተለይ በቤላሻንጉል የነበሩ መሪዎች ከአዲሶቹ እንግዶች ጋር በመቀራረብ ልጆቻቸዉን ለአረቦች መዳራቸዉ የበርታን ወግ በሰፊዉ እንደለመዱ ይናገራል፡፡

ስለዚህ ከበርታና ከአረብ እንዲሁም ከፉኝና ከአረብ የተዳቀለ በበርታ ባህልና ቋንቋ የተካነ አዲስ ሌላ ትዉልድ መፈጠር ጀመረ፡፡ ይህ አዲስ ትዉልድ "መዩ" ተብሎ ይታወቃል፡፡ በበርተኛ ቋንቋ "መዩ" ማለት ተወላጅ ማለት ነዉ፡፡ "ቀደም ሲል የፉኝ መጤዎች እንዳደረጉት ሁሉ አረቦች ከአገሬው ህዝብ ጋር የተቀራረቡት ሰላማዊ በሆነ መንገድ ነዉ፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ ሕዝቦች በመጀመሪያ አሰፋፈራቸዉ የበርታ ባላባቶች መኖሪያ አከባቢ በመስፈር ያላቸዉን ስልጣኔና የንግድ ዕዉቀት በመጠቀም ከበርታዎች ጋር በመቀራረብና በመግባባት ኖረዋል፡፡ከበርታ መሪዎች ጋር የጋብቻ ትስስር በመፍጠር በአጭር ጊዜ ዉስጥ የስልጣን በትር በእጃቸዉ ሊያስገቡ ችለዋል፡፡

## 1.2 የጉምዝ ብሔረሰብ ጥንተ ታሪክና ምንጭ

የጉምዝ ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ እንደብሄረሰቡ አባቶችና አፈ-ታሪክ ጥንታዊ መኖሪያቸዉ በዋናነት ጎንደርና አካባቢው፣ ጎጃም እና ጣና ሐይቅ አካባቢ ለብዙ ዘመናት ይኑሩ እንደነበረ

ይገልፃሉ፡፡ መተዳደሪያቸውም የተለያዩ የሰብል ምርቶች በማምረትና በተጨማሪም ጥጥ፣ ትምባሆ፣ ዝንጅብል፣ ለውዝና ሰሊጥ ሲያመርቱና ሲጠቀሙ ነበረ፡፡ እንዲሁም በተጓዳኝ አደንና ዓሣ እያሰገሩ ሲኖሩ እንደነበረ አፈ-ታሪኮች ይናገራሉ፡፡ በተጨማሪም አሰፋፈራቸዉ ጎሳዊና ንዑስ ጎሳዎች ሆኖ ነገር ግን ጠቅላላ በአንድ ትልቅ እንደንጉስ በሚያምኑት "ኩሳ" በሚባል የብሄረሰቡ መሪ ይተዳደሩ እንደነበር ይገለፃል፡፡ የብሔረሰቡ ስም ስያሜም "ጉምዝ" ይባል እንደነበር ይናገራል፡፡ ይሁን እንጂ በወቅቱ በነበሩት ገዢ መደቦች በተደጋጋሚ በደረሰባቸው ጦርነት ምክንያት አሁን ወደ አሉበት ቆላማ ቦታዎች ማለትም ከጎንደርና ከጐጃም እንዲሁም ከወለጋ ቆላማ ሰፍራዎች ተገፍተውና ተሰድዶው እንደመጡ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

የቋንቋ አጥኚዎች እንደሚገልፁ የጉምዝ ብሄረሰብ በቋንቋ ደረጃ የናሎ-ሰሃራ ቋንቋ ቤተሰብ የሚመደብ ሲሆን ቋንቋውም በኮሞዋን ቋንቋ ተናጋሪዎች ምድብ ውስጥ የሚመድብ ነው፡፡ አሰፋፈራቸውም የአባይ፣ በለስ፣ ዲንደር፣ ሹንፋና ታች ተካዜ ወንዞችን ተከትሎ የሚኖርና በቀድሞ መንግስታት አገዛዝ ወቅት በጎንደርና ጉጃም ክፍለ ሀገር ስር የሚተዳደር ብሄረሰብ ነበር፡፡

በደርግ ዘመን መንግስት በጎንደር የመተማ አካባቢ ራስ ገዝ እንዲሁም በጉጃም ክፍለ ሃገር ደግሞ የመተከል አካባቢ ራስ ገዝ እንዲሆኑ ማለትም ብሄረሰቡ ራሱን በራሱ እንዲያሰተዳደር የተደረገ ቢሆንም ነገር ግን በተጨባጭ ሲታይ ራስ ገዝ አሰተዳደሮቹ የብሄረሰቡ ሳይሆኑ ሌሎች መልሰው ሲያሰተዳደሩ እንደነበረ ታሪካዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ታሪካዊ ዶክመንቶች እንደሚያስረዱት የጉምዝ ብሄረሰብ አመጣጡ ከካናአን /ሃም/የኖሃ ልጅ ሲሆን ከቀደምት ነዋሪ ጥቁር አፍሪካ የሚመደብና ለብዙ ዘመናት በኢትዩጵያ የኖረ ብሄረሰብ ነዉ፡፡ ብሄረሰቡ በ"ኩሳ" አሰተዳደር ዘመን ሶስት ጎሳዎች በተለያዩ ጊዜያት ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል ይላል፡፡ እነሱም ጉምዝ፣ ቅማንት እና ወይጦ ሲሆኑ የዘር ግንዳቸዉም ሲኒ፣ አረዋዲ እና ሳምሪ ይባላሉ፡፡

በሌላ መንገድ አንዳንድ ፀሐፊዎች እንደሚሉት የጉምዝ ብሄረሰብ ቀድምት የጥቁር አፍሪካ ህዝብ ዘር ነው፡፡ ስለዚህ የጉምዝ ብሄረሰብ በአንድ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ ገባ የሚለውን ሀሳብ ይቃወማሉ፡፡ የጉሙዝ ብሄረሰብ አብዛኛዉ አርቢና ለእንስሳቱ የሳር ግጦሽ ፍለጋ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ የሚኖር እና ጥቂቶቹ ደግሞ በቋሚ እርሻ ሥራ የተሠማሩ ሲሆን በዘመኑ "ኩሳ" በሚባል ጎሳቸው ይገብሩ እንደነበር ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ ከጎንደርና ጉጃም ደጋማ ስፍራ ለ440 ዓመታት ሲኖሩ ቆይቶ ነገር ግን በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያና በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ኩሳና ጎሳዎቹ ተሸንፈው አሁን ወደ አሉበት የኢትዮጵያ ቆላማና ሞቃታማ አከባቢዎች ለመሰደድ እንደተገደዱ ይገለፃሉ፡፡

ጥንታዊ ጽሑፎች እንደሚገልጹት እነዚህ የጉምዝ ሕዝቦች በገዥ መደቦች መስፋፋት ለባርነት ስዳረጉ እንደነበረ ይገልጻሉ፡፡ በዚህ ምክንያት የናይሎ-ሰሃራን ጎሳዎች ወደ ቆላማዉ የሱዳን ጠረፍና ሙቀታማ አከባቢዎች እስከ ቤኒሻንጉል አካባቢ ተሰድደዋል ይላሉ፡፡

አብዛኛዉ የኢትጵያ ታሪክ ፀሐፊዎች የጉምዝን ታሪክ ለመፃፍ ትኩረት አልሰጡም፡፡ የፃፉትም በራሳቸዉ እና በአስተርጓሚዎቻቸዉ ስለጉምዝ ብሄረሰብ አመጣጥና አሰፋፈር ትክክለኛ መረጃ ሳያገኙና ሳያረጋግጡ ለመፃፍ ሞክረዋል፡፡ይህ ደግሞ ትክክል አይደለም ምክንያቱም ያለመረጃ የሚፃፈው ታሪክ የተዛባ ይሆናል፡፡

በቋንቋ ደረጃ የጉምዝ ብሄረሰብ በናይሎ-ሳራ የቋንቋ ዘር ግንድ የሚመደብና ኮሞዋን ቋንቋ ቤተሰብ ተናጋሪ እንደሆነ የቋንቋ አጥኞች ይገልጻሉ፡፡ በሌላ በኩል በአካባቢ ጐሣ መሪዎች ለረጅም ጊዜ

ስተዳደሩ እንደነበረ የአገር ውስጥና ውጭ አገር ታሪክ ፀሐፊዎች ሲያደባብሱት እንደነበር እና የገገር መደቦች በጉምዝ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ በደል ሲያደርሱበትና ሲሰደድ የነበረ ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡

ሌላው የጉምዝ ብሄረሰብና ህዝብ ታሪካዊ አመጣጥ መልካም ወግ ባህሉና እሴቶቹ የገገር መደብ ሰርዓቶች ሊፃፍ አልፈቀዱም፡፡ በአንፃሩ ደግሞ አንዳንዶች የጉምዝ ህዝብ ታሪካዊ አመጣጡ ፃፍን የሚሉት ፀሃፊዎች የገገር መደቦቻቸው ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ ሲፅፉ እንደነበሩ ከላይ የዉጭ አገር ተወላጆች ሳይቀር በተለይ ከኢህአዴግ መንግስት ምሥረታ በኋላ አዳዲስ የታሪክ ፀሃፊዎች ትክክለኛ የጉምዝ ህዝብ ታሪክን ለመፃፍ የጀመሩ መሆኑን ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦቻቸዉ መረዳት ይቻላል ፡፡

ያም ሆነ ይህ ያለፈው ዘመን የጉምዝ ብሄረሰብ ሲደረሰበት የነበረው ብሄራዊ ጭቁና አሜን ብሎ የተቀበለ ህዝብ ሳይሆን ራሳቸውን ከጭቆና ነፃ ለማወጣት ለብዙ ዘመናት በግልም ሆነ በተደራጀ መንገድ ሆኖ ሲታገል መቆየቱና በተለይም የደርግ መንግስት በኢህአዴግ ሠራዊት ሊደመሰስ በተቃረበበት ወቅት የጉምዝ ህዝብ ወንድም ከሆነው የበርታ፣ የኮሞ፣ ማኦና ሽናሻ ህዝብ ጋር በመሆን ልጆቻቸው በማዋጣት ኢህአዴግ ሠራዊት ጎን በማሰለፍና በመዋጋት አሰተዋፅኦ ማድረጉ የሚረሳ ታሪክ አይደለም፡፡

ሌላ ጊዜም ቢሆን ኢትዩጵያ አገራችን በተለያዩ የዉጭ መንግስታት በተወረረበት ወቅት ሀገሩን ከወራሪ ለመታደግ እንደማንኛውም የኢትዩጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጦርና ጋሻ ሰብቀው በጦርነቱ ላይ የተሳተፈ ህዝብ ነው ፡፡ ይህ ሃቅ እያለ ግን ባለፉት መንግሥታት የጉምዝን ህዝብ ከኢትዮጵያዊነት ለማራቅና ለዘላዓለም በፍፁም በባርነት ቀንበር ስር እንዲዉደቅላቸው የተጠቀሙበትን አዋራጅ ስም ሲሰጣቸው ነበረ፡፡

### ስያሜና አሰፋፈር

የብሄረሰቡ ስም ስያሜ በተመለከተ ጉምዝ ሲሆን ትርጉሙም ጉዪንዛ/ጉንዛ/ ወይም ወንድ ከሚል የብሄረሰቡ ቃል የተዉሰደ ነው ብሎ የብሄረሰቡ አዛወንቶች ይናገራሉ፡፡

የጉምዝ ብሄረሰብ እንደማንኛዉም የኢትዩጵያ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በአገሪቱ ዉስጥ በተፈጥረው ምቹ ሁኔታ እራስን በራስ የማስተዳደር መብት በመጠቀም ወንድም ከሆኑት የበርታ፣የሽናሻ፣የማኦ እና የኮሞ ሕዝቦች ጋር በመሆን በ1985 ዓ/ም የራሳቸው ክልል መስርቷል፡፡ በዚህም መሠረት የጉምዝ ብሔረሰብ በ3ቱም የክልሉ ዞኖች የሚገኝ ሲሆን በዋናነት ግን በካማሽና በመተከል ዞኖች ዉስጥ በ11 ወረዳዎች ተድራጅቶ ራሱን እያሰተዳደረ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ የብሔረሰቡ የሕዝብ ብዛት በ1999 ዓ/ም በተደረገዉ አገራዊ የህዝብና የቤት ቆጠራ 163,781 ሲሆን አሰፋፈሩም በምስራቅና ሰሜን ከአማራ ክልል፣ በምዕራብ ሱዳን፣ በደቡብ ደግሞ የአሶሳ ዞንን በምዕራባዊ ደቡብ ደግሞ ከምስራቅና ምዕራብ ወለጋ (ኦሮሚያ ክልል) ያዋስናል፡፡ በተጨማሪም የብሔረሰቡ ሕዝብ በአማራ ክልል፣ በትግራይ ክልልና በኦሮሚያ ክልል በርካታ አከባቢዎች ላይ ሰፍሮ እየኖረ ይገኛል፡፡ የጉምዝ ህዝብ አሁን በሚኖርባቸው ወረዳና ቀበሌዎች አሰፈላጊ የማህበራዊ ኢኮሚያዊ መሠረተ ልማቶች ከሞላ ጎደል የተሟላ ሲሆን ህዝቡም ራሱን ከደህነት ለመዉጣት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እየተጋ ኑሮውን በተቻለ መጠን እያሻሻለ ይገኛል ፡፡

የጉምዝ ሕዝብ አሰፋፈር በጥንት ጊዜ በነበረ ሁኔታ ስንመለከተዉ አሰፋፈሩ የመጀመሪያ ዓላማዉ ጠላትን ለመከላከል የሚያስችል ቦታ ይመረጣል፡፡ በዚህም መሠረት ቦታዉ የጠላት እንቅስቃሴ በሩቅ እይታ መቆጣጠር የሚያስችል ከፍታ ያላቸዉ ተራሮች ወይም ከጠላት እይታ የተሰወረ ጥቅጥቅ ያለ ደን ያለበት አካባቢ ሲመረጥ ሌላኛው ዓላማዉ ለእርሻና አደን ምቹ ቦታ ይመርጣል ፡፡ በተጨማሪም የዉሃ መገኛ የቤት ሣር ክዳን የሚገኝበት አካባቢ መስፈር ይመርጣል፡፡

ጉምዞች ወንዝን ተከትሎ የሚሰፍሩበት ብዙ ምክንያቶች ቢኖርም ዋናዎቹ ምክንያቶች  የመጠጥ ዉሃ በቅርበት ለማግኘትና  ዓሳ ለማስገር  እንደነበረ የብሄረሰቡ አባቶች ይገልፃሉ፡፡

የጉሙዝ ሕዝብ አሰፋፈር የሚመሠርተዉ ንዑስ ጎሳዉን ይዞ ነው፡፡ በተጨማሪም ደግሞ የቅርብ ዝምድና ካላቸዉ ለምሳሌ ከአምቻ/ልጅ ባል/ የእህትማማቾችና አጎት ልጆች በአንድ አከባቢ ቤታቸዉን በማቀራረብ ወይም በተጠጋጋ ሁኔታ ይሰራሉ ፡፡ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ማህበራዊ ኑሯቸዉ እንዳይላላ ሰለሚያሰቡና በብሄረሰቡ ባህል ጎሮቤታሞች እራትና ቁርስ አብሮ የመብላት ባህል እንዲሁም የአዝመራና ሌሎችም ሥራዎች በጋራ ለማከናወን እንደነበረ ይገልፃሉ፡፡

ሌላኛው ምክንያት በብሄረሰቡ አባላት እምነት ብዙ ጊዜ በንዑስ ጎሳዎች መካከል የተለያዩ ግጭቶች ሲከሰቱ በህይወት የመጠፋፋት ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል የደም ብቀላ ስላለ የአንድ ንዑስ ጎሳ አባል ሄዶ ወደ ሌላ ንዑስ ጎሳ መንደር  ተቀላቅሎ ለመኖር ስለሚሰጋ ከዘመዶቹ ጋር መስፈርን ይመረጣል፡፡

የቤት ሥራዉና የእርሻ ሥራዉ የሚከናወነዉ በህብረት ሲሆን ስርዓቱም የቤተዘመዶች ደቦ በማዉጣት ተራ በተራ የደቦ ቦርዴ/ጠላ እየተጠመቀ ይከናወናል፡፡ ስርዓቱም የቤተዘመዶቹ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባርና አንድነትን ያጠናክራል ብሎ ያምናሉ፡፡

የብሄረሰቡ አባቶች አገላለፅ መሠረት አብዛኛው የጉምዝ ብሄረሰብ  የአባይን ወንዝ ተከትሎ የሰፈረ ሲሆን ይህም ከአማራ ክልል የጓጉሳ ወምበርማ መነሻ አድርጎ የአባይ ወንዝ ግራና ቀኝ የኦሮሚያ ክልል ምስራቅና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች ወረዳዎችና ተጎራብቶ እሰከ ታችኛው ሱዳን ድንበር ድረስ ይዘልቃል፡፡ ሌላው የድዴሳና የአንገር ድዴሳ ወንዞችን ተከትሎ ዳቡሰን ተሻግሮ የአሶሳ ዞን የኦዳ ቡልዲግሉ፣ የመንጌናየ ሸርቆሌ ወረዳዎችን ይጎራበታል፡፡ ሌላኛው አሰፋፈር የካማሺ ዞን አምስቱ ወረዳዎች የያዘ ሲሆን ከኦሮሞና ከበርታ ህዝብ ጋር አንዳንድ ቦታዎች ላይ ተቀላቅሎ ይኖራል፡፡

በመተከል ዞን የአባይን ወንዝ ግራ መሰመር ይዘው መነሻው የአማራ ክልል ጓጉሳ ወምበርማ ወረዳ ጀምሮ እሰከ ባምቡዲ ወይም ሱዳን ጠረፍ  ድረስ ይደረሳል፡፡ መሃሉ ደግሞ የበለስና ግልግል በለስ ወንዞችን ግራና ቀኝ ይዘው በተመሳሳይ እሰከ ሱዳን ደምበር ሰፍረዋል፡፡ ሌላው የጉምዝ ሕዝብ የዲንድር ወንዝን ተከትለው እስከ ቋራ ከሚባል የአማራ ክልል ወረዳ በማዋስን ሱዳን ደንበር ጠረፍ ሰፍረዋል፡፡ በምስራቅ በአማራ ክልል የአዊ ዞን ወረዳዎችን በሰሜን በአማራ ክልል የሰሜን ጎንደር ዞን እና በምዕራብ ሱዳን እንዲሁም በደቡብ የዓባይ ወንዝ ወይም የከማሺና የአሶሳ ዞንና ወረዳዎችን ሲያዋስን ህዝቡ ከአማራ፣ ከአገው፣ ከሺናሻ፣ ከበርታና ከፉኝ ህዝብ ጋር በአብዛኛው ቦታዎች ተቀላቅሎ የሚኖር ሲሆን ከሱዳን ህዝብ ጋር ደግሞ ይጎራበታል፡፡

ሌላው የጉምዝ ህዝብ የሰፈረው በአማራ ክልል በሰሜን ጎንደር ዞን በመተማ፣ ማጠበያ፣ ቋራ፣ ታች አርማጭሆ፣ ወልቃይት ፀገዴ ወደግምዙዋ በሚባሉ ወረዳዎችና አካባቢዎች ሰፈረው የሚገኙ ሲሆን አብዛኛው ህዝብ የሹንፋን ወንዝ ከላይ እሰከ ሱዳን ድንበር ድረስ ተከትሎ ሰፍረዋል፡፡ የሚዋስኑት ደግሞ በምስራቅ ከአማራ፣ በሰሜን ከትግራይ፣ በደቡብ የመተከል ዞን ዳንጉርና ጉባ ወረዳዎች ሲሆን በምዕራብ ከሱዳን ህዝብ ጋር ይጎራበታል/ይዋስናል/፡፡ እንዲሁም የጉምዝ ህዝብ በተጎራባች የሱዳን

ግዛቶች ውስጥ በብዛት ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ በደማዚን፣ ረሴርስ፣ ለከንዲ፣ ኮረኮጀ፣ ዲንድር፣ ሲናር እና ታያ፣ በሚባሉ አካባቢዎች እንዲሁም በግብፅ ዉስጥ ኑቢያ በሚባል ግዛት ዉስጥ ስፈረው ይገኛሉ፡፡

### 1.3 የቦሮ-ሺናሻ ብሄረሰብ ጥንተ ታሪክና ምንጭ

ዛሬ በሀገራችን የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦቸ ባህል፣ ቋንቋና ታሪክ ተጠብቆና ዳብሮ እንዲቆይ፣ እንዲሁም በፅሁፍና በሌላም መንገድ ለትውልድ እንዲተላለፍ ይበረታታል፡፡

በሌላ በኩል እንደማንኛውም ህዝብ የቦሮ-ሺናሻ ህዝብም የራሳቸው የሆነ ታሪካዊ አመጣጥና ምንጭ እንዲሁም አሰፋፈር፣ ባህል፣ ቋንቋና ታሪክ ያላቸው መሆኑ ታሪካቸው በሚገባ መታወቅ ያለበት ያደርገዋል፡፡ በዚሁ መሰረት የቦሮ-ሺናሻ ብሔረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ ምሁራን በሁለት መንገድ ይገልጹታል፡፡ ይኸም አንዱ አገላለጽ፡ በቅድመ-ታሪክ ከእስራኤል፡ ምድር ግብፅን አቋርጠው እንደመጡና ሁለተኛው አገላለጽ ደግሞ በኢትዮጵያ ቀደምትና ነባር ነዋሪዎች እንደሆኑ ይገልጻሉ፡፡

የመጀመሪያውን አገላለጽ በተመለከተ በብሄረሰቡ አባቶች በአፈ-ታሪክ ሲወራረስ የመጣውን አመጣጣቸውን ሲገልጹ፡-ቦሮ-ሺናሻ የተፈጠረውና የተወለደው ከከንዓን ምድር (የዛሬዋ እስራኤል) ሲሆን ከዚያም ከከንዓን ምድር ፈልሰው ወደ ግብፅ ምድር እንደገቡና በዚህም ቆይታቸው ከግብፅ ምድር የመድሐኒት እና የልዩ ልዩ እውቀቶችና ክህሎቶችን እንደለመዱና ለም የሆነ የግጦሽ እና የእርሻ መሬት ፍለጋ ሲሉ በጥንት ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ምድር ገብተው እንደተሰራጩ የብሄረሰቡ አባቶች ይገልጻሉ፡፡

ሁለተኛውን አገላለፅ የታሪክ ፀሐፊዎች እንደሚገልጹት የቦሮ-ሺናሻ ብሔረሰብ ምንጩ ደቡብ ኢትዮጵያ እንደሆነና የኦሞቲክ ቋንቋ ተናጋሪ መሆኑን በመግለፅ ዛሬ ወደ አሉበት ቦታዎች የመሠራጨቱ ምክንያትም በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው የህዝብ ንቅናቄና እና የደጋው ኢትዮጵያ ክርስትያናዊ መንግስት (The Christian Highland State) መስፋፋት ነበረ ይባላል፡፡

ከዚህም ባሻገር በሌላ አገላለጽ ምሁራን ቦሮ-ሺናሻ ከሌሎች የጎንጋ ህዝቦች (ካፊቾ፣ ሻክቾ እና ሌሎችም) ጋር ጠንካራ ተመሣሣይ ታሪካዊ ግንኙነት እና የጋራ ምንጭ ያላቸው መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ የዚህ እውነታ ሲረጋገጥ በቅርቡ በቦሮ-ሺናሻ፡ በካፋ እና በሻካ ህዝቦች መካከል የጋራ ግንኙነት መድረክ ተፈጥሮ የእነዚህ ህዝቦች ምንጭ፣ ባህል እና ቋንቋ ተመሣሣይ መሆን ታሪካዊ ትስስር መኖሩን ያረጋግጣል፡፡

### የቦሮ-ሺናሻ ብሄረሰብ ስያሜና አሰፋፈር

የቦሮ-ሺናሻ ብሔረሰብ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ከሚገኙት አምስቱ ነባር ህዝቦች መካከል አንዱ እና የቀድሞ መጠሪያው "ቦሮ/Boro" ሲባል መጠሪያውንም ያገኘው "ቦሪ/Bori" ከሚባለው የብሔረሰቡ አባት እንደነበረ የብሔረሰቡ የእድሜ ባለፀጋዎች ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን በብዛት ህዝቡ የሚታወቀውና የሚጠራው ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔር-ብሔረሰቦችና ህዝቦች "ሺናሻ" በመባል ነው፡፡ ይህም ዛሬ የሚጠራበትን ስያሜ ያሰገኘው ብሔረሰቡ በቅድመ-ታሪክ ዘመን በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በተንቀሣቀሰበትና በሰፈሩበት ወቅት ነበረ፡፡ ይህም ጎጃም ውስጥ ዳሞት የሚባል ቦታ በብዛት ለመስፈር በተንቀሳቀሱ ጊዜ በወቅቱ በቦታው ይኖሩ የነበሩ ህዝቦች በእንግዶቹ ቁጥር

መብዛት ተደናግጠው *"ሺ እና ሺ ቁጥር ህዝብ ሊወረን መጣ"* በማለታቸው በዚህ ምክንያት ብሔረሰቡ ሺናሻ የሚለውን ስያሜ እንደወረሰ የብሔረሰቡ የእድሜ ባለፀጎች ይገልፃሉ፡፡

ከዚህ በመነሳት ከላይ ከተሰጡ ስያሜዎች በአሁኑ ጊዜ ብሄረሰቡ በብዛት የሚታወቀውና መጠሪያው "ቦሮ-ሺናሻ" የሚለው ሲሆን ለዚህም ዋናው ምክንያት "ቦሮ" በብሄረሰቡ የሚታመንበት የቀደምት የብሄረሰቡ መጠሪያ እንደሆነ በመሆኑና "ሺናሻ" የሚለው ደግሞ ለረጅም ዘመናት ብሄረሰቡ በሌሎች ብሄረሰቦች ሲጠራ የነበረ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ብሄረሰቡ "ሲንቾ" ፤ "ዳንጋቦ" እና "ጎንጋ" በመባልም ይጠራል፡፡

በአሁኑ ሰዓት የቦሮ-ሺናሻ ህዝብ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በመተከል ዞን (በወንበራ፣ ቡለን፣ ድባጢ፣ ዳንጉር እና ጉባ ወረዳዎች) እና በአሶሳና ግልገል በለስ ከተሞች ሰፋሮ ከሚገኙ ህዝቦች አንዱ ነው፡፡ የህዝቡ ቁጥር በ1999 ዓ.ም በተደረገው ህዝብና ቤት ቆጠራ መሠረት 52,637 እንደሆነና ዛሬ ግን ይህ ቁጥር በክልሉ ድረ-ገጽ ላይ እንደሚያሳየው 60,587 እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ከዚህም ውስጥ 84% ያህሉ በገጠሩ አካባቢ እና 16% ያህሉ በከተማዎች እንደሚኖር ያሣያል፡፡

እንደ ቋንቋ እጥኝዎች አመዳደብ የብሔረሰቡ ቋንቋ የጎንጋ ቋንቋ ተናገሪ ቡድን ውስጥ የሚመደብ ሲሆን ቋንቋውም "ቦሪ ኖኖ"/ሺናሽኛ ይባላል ፡፡

ጥንታዊ የብሔረሰቡ የአሰፋፈር ሁኔታ ስንመለከት በተለያዩ ምሁራን በተለያየ ሁኔታ እንደሚገለፅ እና ትክክለኛ የሆነ የአሰፋፈር ሂደት ግን ማወቅ አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ለዚህም እንደ ምክንያት የሚገለፁት፡-

- አንደኛ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ቦሮ-ሺናሻ የራሱ የሆነ አፃፃፍ ፊደል ያልነበረውና የራሣቸው የመረጃ አያያዝ ሥርዓት አለመኖሩ የብሔረሰቡን ታሪክና ባህሉን በጽሑፍ ለማቆየት አስቸግሯል፡፡
- ሁለተኛው በብሔረሰቡ ውስጥ ጥልቀት ያለው ጥናት ብሔረሰቡ ላይ ያካሐዱ የብሔረሰቡ ልጆች በቀደምት ታሪክ ውስጥ ያልነበሩ መሆኑ፣
- ሶስተኛው ቀደም በባለፉት ሥርዓቶች የነበሩ የኢትዮጵያ ነገስታት ለብሔረሰቡ ማንነት፤ መከበርና መጠናት ትኩረት የሰጠ አለመሆኑ፤
- አራተኛው ከላይ በተገለፁት እውነታዎች ምክንያት በቦሮ-ሺናሻ ብሔረሰብ ታሪክ ላይ የተፃፉም ቢኖሩም የተዛቡ፣ ትክክለኛነቱን የሳቱ እና ዓላማቸውም ግልፅ ያልሆኑ ጽሑፎች መኖራቸው በዋናነት ይገለፃሉ፡፡

ምንም እንኳን ከላይ የተገለፁት ችግሮች ቢኖሩም በህዝብ ውስጥ እና በአንደንድ ምሁራን ስለብሔረሰቡ የቀደምት አሰፋፈር ሂደት በተለያየ መልኩ ለመግለፅ ተሞክረዋል ፡፡

የብሔረሰቡ አባቶች የቀደምት የአሰፋፈር ሂደት ሲገለጹ በምዕራብ ከሱዳን ድንበር እስከ ጫራ፤ በሰሜን ቋራ፣ ሊሙ፣ አሙሩ፣ ጊዳ እና ሆሮ-ጉድሩ በሰሜን ምስራቅ ወለጋ እስከ ደቡብ ወለጋ ማለት ዴዴሣ ሸለቆ ድረስ እንደሰፋሩ እና እንዲሁም እስከ ጎጃም እና መተከል ምሥራቃዊ ዱራ ወንዝ ድረስ እንደነበር ይገልፃሉ፡፡

አንዳንድ የታሪክ መዛግብት እንደሚያሳዩት የጎንጋ/ሺናሻ ህዝቦች ሰፊ ግዛት የነበራቸውና በዚህም ግዛት ውስጥ ማንነታቸውን፤ ባህላቸውንና ወጋቸውን ጠብቀው እንዳይኖሩና የሌሎችን ባህል እንዲከተሉ ጥቂቶችም ወደ ሌሎች አካባቢዎች እንዲሰራጩ፥ የደጋው ኢትዮጵያ ክርስትያናዊ

መንግስት (The Christian Highland State) እና በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነበረው የሕዝብ ንቅናቄ ምክንያት አብዛኛው የቦሮ-ሺናሻ ህዝብ በአብዛኛው በመተከል አካባቢ ተሰራጭቷል፡፡

ይህንን አገላለፅ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ ሁኔታ ይገልፃሉ፡፡ ይህም እንደሚገልፁት ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ከደቡብ ጎጃም እስከ ደቡብ ምዕራብ ደጋማ ቦታዎች ሀያል የሆነ የጎንጋ ሥርዓት-መንግስት (Kingdom) መስርተው እንደነበረና ይህም ጠንካራ መንግስት በወቅቱ የነበረው የሕዝብ ንቅናቄ/ግፊት ምክንያት በሶስት(ደቡብ ጎንጋ፣ ማዕከላዊ ጎንጋ እና ሰሜን ጎንጋ) ሆነው እንደተከፋፈሉ እና ከደቡብ ጎንጋ የተገነጠሉ የሰሜን ጎንጋ ህዝቦች/ሺናሻ/ እንደሆኑ ይጠቁማሉ፡፡

አንዳንድ የታሪክ ፀሐፊወች እንደሚገልጹት የሆሮ-ጉዱሩ አካባቢ ቀደምት ነዋሪዎች የቦሮ-ሺናሻ ህዝብ መሆናቸውን ከመግለፁም በተጨማሪ በዛ ያሉ የቦሮ-ሺናሻ ህዝብ በአሙሩ እና ጊዳ አካባቢዎች እንደነበሩ በመግለፅ ከዚያም ጋር አያይዞው የዓባይን ወንዝ በመሻገር በመተከል አካባቢ እንደሰፈሩ ይገልፃል፡፡

ይሁን እንጂ የደጋው ኢትዮጵያ ክርስትያናዊ መንግስት (The Christian Highland State) ነገስታት የወርቅ ማዕድን ፍለጋ በሚያደርጉት ጥረት የሺናሻ ህዝብ የሚኖርባቸው አካባቢዎች ወረራ በማካሄድ በህዝቡ ላይ የበላይነት ማሳየት እንደቻሉ የታሪክ ፀሐፊዎች በጽሁፋቸው ይገልፃሉ፡፡

በተጨማሪም እነዚህ ፀሐፊዎች እንደሚያስረዱት በኢትዮጵያ በነገሥታት ዘመን በተለያየ ጊዜ የመተከል አካባቢን የሚንድ ወረራ እንደ አካሄዱና የሺናሻና የጉሙዝ ህዝብን የሚመሩ ከሌላ ብሄረሰብ በማምጣት መሪዎችን እንደሾሙባቻው ጽፏል::

በሌላ በኩል እ.ኤ.አ. በ1570ዎቹ ተከታታይ በሆነ የህዝብ ንቅናቄ ምክንያት ምሥራቅ ጎጃም፣ ዳሞት፣ አጋው ምድር እና እንዲሁም በሺናሻ እና በጉሙዝ የተያዙ የመተከል አካባቢዎች ላይ ወረራ አካሂደዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ሺናሻ ህዝብ ወደ ቀሪው የቆላማ ቦታዎች እንደተሰራጩ ታሪካዊ ዶክመንቶች ይገልፃሉ፡፡

በ17ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና 18ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ በነበረው የደጋው ኢትዮጵያ ክርስትያናዊ መንግስት (The Christian Highland State) ጫና ከፍተኛ ቁጥር ያለው የጎንጋ ህዝብ ከነበረው ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ወደ ሰሜን ምዕራብ እንደገቡ አጥኚዎች ጠቅሶቷል፡፡

የብሄረሰቡ አባቶች እንደሚገልጹት ከጎንጋ መንግስት መፍረስ በኋላ የጎንጋ ህዝቦች ወደ ተለያየ አቅጣጫ ሲበታተኑ ከእነሱ አንዱ የሆነው ቡድን ዛሬ የቦሮ-ሺናሻ ህዝብ ወደ ሚገኝባቸው የሰሜን-ምዕራብ ኢትዮጵያ ክፍል በተለያዩ ቦታዎች እንድሰፈሩ ይናገራሉ፡፡

የቦሮ-ሺናሻ ብሄረሰብ በዋነኝነት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት በመተከል ዞን በሚገኙ በወምበራ፣ በቡለን፣ በድባጤ፣ በዳንጉርና በጉባ ወረዳዎች እና እንዲሁም በአሶሳና ግልገል በለስ ከተሞች እና በሌሎችም የአማራና ኦሮሚያ ክልሎች ይገኛል፡፡

### 1.4 የማኦ ብሔረሰብ ጥንተ-ታሪክና ምንጭ

የታሪክ መረጃዎች እንደሚገልፁት በ18ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዉስጥ ከሚኖሩት ነጋዴዎች ማኦ አንዱ መሆኑና በጥንታዊ የጋርዮሽ ስርዓት ወቅት እንደነበሩ ይጠቅሳሉ፡፡

በ18ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የፉኝ መኳንታዊ መንግስት ተቋቁሞ የነበረ ሲሆን የፉኝ መንግሰት ንጉሱም የሚጠራዉ “መኪ” ተብሎ የሚጠራ የፉኝ ቃል ነበረ፡፡ በወቅቱ በፉኝ ኪንግደም ከተቋቋሙት የመንግስት ክፍሎች ዉስጥ የማኦ መሪ “ኪርኝ” በመባል ይታወቅ እንደነበረ ይገልጻል፡፡

በመሆኑም የአረብ ነጋዴዎች በምዕራቡ አቅጣጫ ወርቅና ሌላ ሀብት ፍለጋ መጥተዉ ከብሔረሰቡ መሪዎች ጋር በመስማማትና በመጋባት የእስልምና ሀይማኖት እንደተስፋፉ ይገለፃል፡፡

በተመሳሳይ የታሪክ አጥኚዎች እንደሚያስቀምጡት በኦሮሚያ አካባቢ ምዕራብ ወለጋ በደቡባዊ ክፍል አንፍሎ አከባቢ ማኦዎች እንደሚገኙና አንፍሎ የሚባል ሲያሜዉ የቦታቸዉ ስያሜ ከመሆኑም በላይ በምዕራብ ወለጋ “ደቡባዊ ማኦ” በመባል ይጠሩ ነበር፡፡

በተጨማሪም ጥናቶች እንደሚያሳዩት የሰሜን ምዕራብ ማኦዎች የናይሎ ሰሃራ ቋንቋ ቤተሰብና የመጀመሪያዉን ይዞ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ህዝቦች በምዕራብ ወለጋ ሱዳን ድንበር አከባቢ የሚኖሩ ህዝቦች እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡

በ17ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን ከፉ ላይ በተደረገዉ በቡሳሴ ጦርነት ተወረው ስለነበሩ የናይሎ ሰሃራ ቋንቋቸዉ ወደ ኦሞቲክ ከተቀየረ በኋላ በ19ኛዉ ክፍለ ዘመን መጨረሻ አከባቢ ደቡባዊ ማኦዎች የመጀመሪያ ቦታቸዉን ለቀው ወደ አንፍሎ እንደሰፋሩ መረጃዎች ያሳያሉ ፡፡

በሰፋሩበት ቦታ ኦሮሞዎች ጋር ሁሌ አብሮ ስለሚኖሩ በመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኦሞቲክ ተቀይሮ የነበረዉ የደቡባዊ ማኦ ቋንቋ በድጋሚ ወደ “ኩሽቲክ ቋንቋ“ ቤተሰብ እንደተቀየረ ይገለፃል፡፡

ታሪካዊ ዶክሜንቶች እንደሚገልፁት በምዕራብ ወለጋ ሲኖሩ የነበሩ ህዝቦች የናይሎ ሰሀራና የኦሞቲክ ቋንቋ ተናጋሪዎች በጥንት የአከባቢዉ ባለቤት እንደነበሩ ያስቀምጣሉ እነሱም፡- ኢጋዲ፣ ግብቶ፣ ካዛ፣ መሰንጎ፣ ሹሉክ፣ ማኦ፣ ደሞቶ፣ ጋንዛ እና ሰንቾ ናቸዉ፡፡

እንደ ጥናቶች አገላለጽ የብሔረሰቡ አመጣጥ ከአፍሪካ ህዝቦች እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ሆኖ በጊቤ አካባቢ ይኖሩ እንደነበረና በነበረዉ ጦርነትና አለመግባባት የተነሳ አካባቢዉን እየለቀቁ ለመበታተን ምክንያት ሆኗል፡፡

በአጠቃላይ የብሄረሰቡ አዛውንቶች እንደሚገልፁ የሕዝቡ ምንጭ በጥንት ሲኖሩ የነበረዉ ከጊቤ እስከ ደማዜን ክምር ድንጋይ ድረስ ይኖሩ እንደነበሩ በመግለጽ በገዥ መደቦች ግዛት መስፋፋት ምክንያት በአሁኑ ጊዜ በየቦታዉ ተበታትኖ እንደሚገኙ ያስረዳሉ፡፡ ማኦዎች ነባሪና ከየትም እንዳልመጡ በመግለጽ በነበረዉ ገዥ መደቦች ስርዓት አከባቢያቸዉን እንደለቀቁ ይናገራሉ፡፡ ፀሀፊዎች በተለያዩ ምክንያት ቋንቋቸዉ መቀየሩን በመግለጽ የቋንቋ ቤተሰብም ወደ ኦሞቲክና ኩሽትክ ተቀይሯል በማለት ሲጽፉ ይታያል፡፡ እዉነታዉ ግን በተለያዩ ምክንያት ብሔረሰቡ

ይበታተን እንጂ የማኦ ብሔረሰብ ቋንቋ ቤተሰብ የናይሎ ሰሃራ ቋንቋ ቤተሰብ እንደሆኑ የብሄረሰቡ አባቶችና ጥናቶች ይገልፃሉ፡፡

## ስያሜና አሰፋፈር

የማኦ ብሔረሰብ እንደማንኛዉም የሀገራችን ህዝብ የራሱ የሆነ ታሪክ ፣ባህል፣ቋንቋ ፣እምነትና ወግ ያለዉ ህዝብ ከመሆኑም በተጨማሪ የራሱ የሆነ አሰፋፈርና ስያሜ ያለዉ ህብረተሰብ ሲሆን መጠሪያው ቀደም ሲል "ሲሸዋላ"፣ "ኪርኝ" እና "ማኦ" በሚል ስም ይጠሩ እንደነበረ የብሄረቡ አዛወንቶች ያስረዳሉ፡፡

"ሲሸዋላ" የሚለዉ መጠሪያ ትርጉሙም ጥቁር ህዝብ ማለት ነዉ፡፡ ሲያሜዉንም ያገኙት ፈጣሪያቸዉ ከሰጣቸዉ የቆዳ ቀለም መንስኤ እንደሆነ የዕድሜ ባለፀጋ የሆኑ አዛወንቶች ያብራራሉ፡፡

በሌላ በኩል ብሔረሰቡ በሰፈረበት አካባቢ ኦሮሞዎች ሲሰፍሩ ማኦ በማለት እንደሰየሚቸዉ እንዲሁም ደጃዝማች ጆቴ ቱሉ ጊዳሚ አካባቢን በመሩበት ወቅት በነበረዉ ጦርነት የተወሰኑ የህብረተሰቡ አባላት/የማኦ አባላት/ ተፈናቅለው በአሶሳና በሸርቆሌ መካከል በሚገኘዉ "ኪርኝ" ተራራ ስር በመጠለላቸዉ ምክንያት በርታዎች በተራራዉ ስም ‹‹ኪርኝ›› በሚል ስያሜ ይጠሯቸዉ እንደነበር ያስረዳሉ ፡፡

ይሁን እንጂ በኪርኝ ተራራና በሌሎች አካባቢዎች ያሉት የበርታ ብሔረሰብ አባላት የኋለ ኋላ "ማኦ" የሚለዉን ስያሜ ይበልጥ እየተጠቀሙበት በመምጣታቸዉ የብሔረሰቡ መጠሪያ ሆኗል፡፡ "ማኦ" ወይም "ሲሹዋላ" በማለት የተለያዩ ስያሜ የተሰጣቸዉ ቢሆንም ትርጉሙ ግን ቆዳ ቀለማቸዉ ጥቁር የሆነ ህዝብ ማለት ነዉ፡፡

በሌላ በኩል የማኦ ህዝብ አሰፋፈር በሱዳንና በሰሜን ምዕራብ ድንበር መካከል ያሉት አካባቢዎች የማኦ ጥንታዊ ሰፍራዎች ነበሩ፡፡ህብረተሰቡ ከነበረው ባህላዊ አኗኗር አኳያ አብዛኛዉን ጊዜ በወንዝ ዳርቻ ጥቅጥቅ ባሉ ጫካዎችና ተራራዎች አካባቢ ይኖር እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የብሄረሰቡ አባላት ይህንን ሀሰብ ሲያጠናክሩ "ኪርኝ" የሚለዉ ስያሜ በሌሎች የተሰጠ ስያሜ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ማኦዎች በተፈጥሮ በሱዳን ጠረፋማ ጫካና ተራራ ዉስጥ የሚኖሩ ጨካኝ ሰዎች ናቸዉ በማለት የተሰጠ ስያሜ ነዉ፡፡ እዉነታዉ ግን ማኦዎች ጫካና ተራራ ዉስጥ የሚኖሩት በገዥ መደቦች ሲደርስባቸዉ የነበረዉን ጭቆና ከራሳቸዉ ለመከላከል ሲሉ እስትራቴጅክ ቦታዎችን ስለሚመርጡ ነዉ፡፡

የብሄረሰቡ አሰፋፈር የተበታተነ ሆኖ መነሻቸዉ ጊቤ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በኦሮሚያ ክልል ዉስጥ በሚገኙ ቦታዎች ቤጊ፣ አንፎሎ፣ ቁንዳላ ወረዳ፣ መነስቡ፣ ነጆ፣ ድዴሳ፣ መተሃራ እንዲሁም በደቡብ ክልል ቦንጋ አካባቢ ይገኛሉ፡፡

እንደጥናታዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት "ቱመት" ከመጀመሪያዉ ማኦዎች እንደነበሩና በበርታዎች እየተገፉ ወደፋዳሲ፣ ቤጊ ፣ባንጋ፣ አንፍሎ፣ ደምብዶሎ፣ ግዳሚና ቡርጅን ተገፍተው እንደሄዱ ያስቀምጣል፡፡

ሲያሜዉም ከማኦ ቋንቋ የተሰጠ ስያሜ እንደሆነ በማስቀመጥ ቱመት ማለት ቱመቶብ ሲሆን ትርጉሙም ዉሃ መጠጣት ነው፡፡ እዉነት የምንናገር ከሆነ ቱመት አካባቢ እንደነበሩና ከቆይታ በኋላ በርታዎች መጥተው እነሱ ጋር እንደተቀላቀሉና ማኦዎችን እንደገፉ ያስቀምጣል፡፡

በተጨማሪም በንጉሥ ዳግማዊ ሚኒሊክ ግዛት ወቅት በሺዎች የሚቆጠሩ ማኦዎች ከባምበሲ ወደ ድዴሳና ደቡባዊ መተሃራ ተሰድደው እንደሰፈሩ በኋላ ግን አብዘኞቹ ማኦዎች ከመተሃራ ወደ ባምባሲ ሲመለሱ ችለዋል፡፡ ይህ ስደት እስከ ደርግ መንግስት ድረስ የነበረ ሲሆን ከደርግ ዉድቀት ወዲህ ማንነቱ ተረጋግጦ ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር ምቹ ሁኔታ በመፈጠሩ ራሳቸዉን ችለው አሁን ወዳለሉበት ስፍራ ማኦ እና ኮሞ ልዩ ወረዳ ራሳቸዉን በራሳቸዉ ማስተዳደር ችለዋል፡፡

በወረዳዉ ህዝቡ በብዛት የሚገኝበት ስፍራዎች ሚሚ ያኮቦ፣ወጼ ወዴሳ ፣ባንጋያቡስ፣ ታርኮ፣ ዜባ ጓቋ፣ ያዓ በልድግስ፣ ቱሉ ዶቆኑ፣ ጉሬ፣ ሽነን ፣ ገደሾላ፣ ፋፋ፣ ሽንቦላ፣ ታጃ፣ ቶንጎ፣ ዋንጋ ጊታን እና ቦቦስ እሽቃባ በብዛት ይገኛሉ፡፡ ሌሎች አካባቢዎችም በአነስተኛ ቁጥር ተሰራጭተዉ ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በአሶሳ ዞን ስር በባምባሲ ወረዳ በከማሽ ዞን በበሎ ጀጋንፎይ ወረዳ ዉስጥ ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ ሌሎች በኦሮሚያ ክልል ጊዳሚ፣ አንፍሎ፣ ቆንዳላና ቤጊ ወረዳዎች እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡ በተለይ በቁንዳላ፣ ጋረርባ፣ ጌሚጋባ፣ ዋናጃ ጪሪ፣ ጅንብላ፣ ሜሻ ቀሽማንዶ፣ ገጃጋጄ፣ ኮንግሎ ጋራኬሎ፣ ሆፋ ፋርጋሽ....ወዘተ ቀበሌዎች ዉስጥ በብዛት ይገኛሉ፡፡

በቤጊ ወረዳ ዉስጥ ብሄረሰቡ የሚገኙባቸው ቦታዎች ቃማ ጫንዲ፤ ኤነ ግርሞስ ዲንቃ አብሻላ፣ ታጃ ሮብ ገበያ፣ ጉንፍ፣ ጸላዱ ጸጋ ቦካ እና ላሎ ኖራ ሲሆን በጊዳሚ ወረዳ ስር የሚገኙ ቀበሌዎች ዉስጥ ደግሞ በግራይ ብሻ፣ ያሎ ቀበሌ እና ሊሙ ቀበሌዎች ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸዉ፡፡

ታሪካዊ መረጃዎች እንደሚገልጹት ብሔረሰቡ ወደ ተለያዩ አከባቢዎች መፍለስና መስፈር ምክንያቶች የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ ያልታረሰ መሬት ፍለጋ ፣ የኦሮሞ ገዥ መደቦች ግዛት መስፋፋት እና የአጎራባች ብሔረሰቦች አሉታዊ ተጽዕኖ ሽሽት እንደነበሩ ይገልፃሉ፡፡

### 1.5. የኮሞ ብሔረሰብ ታሪክና፣ ምንጭ

የቋንቋ አጥኚዎች እንደሚገልፁ የኮሞ ብሄረሰብ በቋንቋ ደረጃ የናሎ-ሰሃራ ቋንቋ ቤተሰብ የሚመደብ ሲሆን የታሪክ መረጃዎች እንደሚገልፁት ኮሞዎች የቀደምት ምንጫቸው በጊያዋ (ጌሚ) ተራራ አካባቢ ነበር ተብሎ ይገመታል፡፡ በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ከጐረቤት ሕዝቦች ግፊት አካባቢያቸውን ለቅቀው ወደ ምዕራብ አቅጣጫ እንደሸሹ ይገለፃል፡፡

ኮሞዎች ራሳቸውን ከነዚህ ሕዝቦች ጥቃት ለመከላከል ሲሉ የቀድሞ መኖሪያ አካባቢያቸውን ለቀው ራሳቸዉን መከላከል ወደሚችሉበት አከባቢ ፍለጋ ምዕራብ አቅጣጫ ወደ ኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ለመሸሽ እንደተገደዱ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በየጊዜው በሚደርስባቸው ባሪያ ፈንጋዮችና አዳኞች ለማምለጥ ሲሉ ብዙ ኮሞዎች በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሥር አስተዳደር ወደ ነበረችው ሱዳን ሲሸሹ ቆይተዋል፡፡ በወቅቱ በሱዳን የነበሩ የእንግሊዞች ቅኝ ግዛት ገዥ አስተዳደር ጥበቃ አድርጎላቸዋል፡፡ በጣሊያን ወረራ ወቅት (ከ1936-1941 እ.ኤ.አ) የባሪያ ንግድ በመከልከሉ ተሰዶ የነበሩት አብዛኛዎቹ ኮሞዎች ወደ ግዛታቸው የተመለሱበት ሁኔታ ነበር፡፡

ፀሀፊዎች በተለያዩ አገላለጽ ከ18ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በኮሞዎችና በገዥ መደቦች መካከል የነበረዉን አለመግባባትና የተደረጉ ጦርነቶች ምክንያት በጥንት ጊዜ ከነበሩበት ቦታዎች ለቆ ራሳቸዉን ከጥቃት ለማከላከል ሲሉ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ስር ወደ ነበረው ሱዳን ጠረፍ አካባቢ እንደሸሹ ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ ኮሞዎች ማንነታቸዉን ለማስከበር ወደኋላ ያሉበት ጊዜ ያልነበረ በመሆኑ ለማንነታቸዉ ሲሉ ከጥንት ጀምሮ እስከ ደርግ ዉድቀት ድረስ በተደራጀና ባልተደረጀ መልኩ ሲታገሉ ነበር፡፡

## አሰፋፈርና ስያሜ

በብሄረሰቡ አባቶች አገላለጽ የኮሞ ስያሜ "ኮም" ከሚል ቋንቋ የተወሰደ ሲሆን ትርጉሙም መተባባር፣ መረዳዳት፣ መተጋገዝ እና አንድ ላይ በማህበር ለችግሩ መፍትሔ ማስገኘት ማለት ነው ብለው ይገለፃሉ፡፡

ኮሞዎች በአጎራባች ብሔረሰቦች በተለያዩ ስም ሲጠሩ ይስተዋላል፡፡ይኸውም ኦሮሞዎች "ኮሞ" ብለው ሲጠሩ፣ ሱዳኖች ደግሞ "ኮማ" ወይም "ኮማን" ብለው ይጠሯቸዉ ነበር፡፡ የኮሞ  የዕድሜ ባለፀጋዎች እንደሚያስረዱት ኮሞዎች "ሚዜ" በመባል የሚታወቅ ተራራ አካባቢ ሲኖሩ እንደነበረ ይገልፃሉ፡፡

ከአጐራባች ብሄረሰቦች በደረሰባቸው ግፊት ምክንያት የነበሩበትን ሚዜ ተራራ ለቀቀው መሸሽ እንደጀመሩና እስከ ቤጊ ድረስ ቄሌም በሚባል ሲንካ አካባቢ እንደተሰደዱ ይገልፃል፡፡ በነዚህ ግፊቶች ምክንያት አሁን ባሉበት ወደ ወዴሣ እና ጃዋ አካባቢዎች በመበታተን እስከ አሁን  ድረስ እየኖሩ ይገኛሉ፡፡ ሌሎች ደገሞ በባንጋ፣ በባፊንቦ፣ በኳንዳፌ እና ኤቢቻ/ጰን ጳሽ/፣ ሻውን፣ ቀራሮ፣ ሉጎ አካባቢ "ኩሚይና  ይጸልቢ" በመሸሽ (በመሄድ) እስከ አሁን ተበታትኖ እየኖሩ ይታወቃሉ፡፡

ብሔረሰቡ በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው እንደሚኖሩ ቢታወቅም በማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ በብዛት ከሚኖሩባቸው ቀበሌዎች ዋና ዋናዎቹ ጉዛ፣ ፋሽሚ፣ ታሻ፣ ይዋ፣ ከዊ፣ ሹማቴ ፣ሜጥ፣ ኤብቻ፣ ማቱሽሜ፣ በዴሳ ሸሬማ፣ ጋንዞ ያንጉ፣ ከሰር፣ ፐንሹብ፣ ዘብሸር እንደሁም በንጋ ተርኮ  ቀበሌዎች በብዛት ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር ያዓ በልዲግስ፣ ሚሚ ያኮቦ፣ ያቡስ ቀበሌዎች የሚኖሩ ሲሆን በክልላችን በአሶሳ ዞን አሶሳ ወረዳ ቡልዳድኔና ቡድር ወዘተ..ቀበሌዎች ይገኛሉ፡፡ ከክልላችን ዉጪ በጋምቤላ ክልልና በሱዳን ጠረፍ ተሰራጭቶ ይገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ አምስቱ ነባር ብሄረሰቦች ባለፉት ስርዓቶች በሀገራችን ተንሰራፍተው በቆዩ አምባገነናዊና ፀረ-ዴሞክራሲ የፖለቲካ ሥርዓቶች የግፍ አገዛዝ የተነሳ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ታፍኖና ማንነታቸው ተረግጦ በመደብና ብሔር ጭቆና ሥር ወድቀው ለከፋ ድህነትና ኋላቀርነት ተዳርገው እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የልማትና የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚ ሳይሆኑ ከመቅረታቸው ባሻገር ለማንነታቸው እውቅና ተነፍጎ በመቆየቱ ባህላቸው፣ ቋንቋቸውና ታሪካቸው እንዳይታወቅና እንዳያድግ ተደርገዋል፡፡ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህዝቦችም እንደ ሌሎቹ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቹ በከፍተኛ ሁኔታ የስርዓቱ ተጎጂዎች የነበሩ ሲሆን በተለይም ነባር ብሔረሰቦቹ ይዞታቸውን በኃይልና በጦርነት እንዲለቁ ተደርጎ በአገራችን የተለያዩ ክፍሎች ተበታትነው እንዲኖሩ እና እየተገፉ በሀገሪቱ ጠረፋማ አካባቢዎች እንዲሰፍሩ ተገድደዋል፡፡ ስለሆነም ቋንቋቸው፣ ባህላቸውና ታሪካቸው ተገቢውን ክብርና እውቅና ተነፍጎት ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ያለፉት ጨቋኝ ሥርዓቶች ሁሉንም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የልማት፣የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች ጥያቄዎቻቸውን የረገጡና ያፈኑ መሆናቸው ሁሉም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ኃይሎች የሚገነዘቡት ሀቅ ቢሆንም በተለይ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህዝቦች ያሳለፉት ጭቆና ግን እጅግ የከፋና የተደራረበ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

# ክፍል ሁለት፡- የክልሉ አጠቃላይ ገጽታ

## 2.1 ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥና የተፈጥሮ ሀብት

በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 31/1995 ዓ.ም መሠረት ክልሉ በሰሜንና ሰሜን ምሥራቅ ከአማራ ክልል፣ በምሥራቅ ከኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ከጋምቤላ ክልል እና በምዕራብ ከሱዳን ጋር ይዋሰናል፡፡ የክልሉ ጠቅላላ የቆዳ ስፋት 50,380 ስኬዌር ኪ/ሜ ስፋት ሲኖረው ከሀገሪቱ አጠቃላይ ስፋት 4.48% ነው፡፡ የአባይ ወንዝ ክልሉን ለሁለት አቋርጦት የሚያልፍ በመሆኑ ክልሉን ለሁለት ከፍሎታል፡፡ ሰሜናዊ ክፍል መተከል ዞን 26,560 ስኬዌር ኪ/ሜ ቆዳ ስፋት ሲኖረው ደቡባዊ ክፍሉ አሶሳ ዞን፣ ካማሺ ዞንና ማኦኮሞ ልዩ ወረዳ በድምሩ 23,820 ስኬዌር ኪ/ሜ ስፋት አላቸው፡፡

ክልሉ ከባህር ወለል በላይ ከ580-2,730 ሜትር ከፍታ ያለው ሲሆን የክልሉ ከፍተኛ ቦታ በዳንጉር ወረዳ የበላያ ፕላቶ እና ዝቅተኛ ቦታዎች የአባይ ሸለቆ ተከትለው የሚገኙ አካባቢዎች ናቸው፡፡ ዋና ዋና የአየር ንብረትም 75 በመቶ ቆላ (ከ1,500 ሜትር በታች) ፣ 24 በመቶ ወይናደጋ (ከ1,500-2,300 ሜትር) እና 1 በመቶ ደጋ (ከ2,300 ሜትር በላይ) ነው፡፡ የክልሉ አማካይ የሙቀት መጠን ከ17 ዲግሪ ሴንቲግሬድ እስከ 29 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሲሆን የዝናብ መጠን ደግሞ ከ860-1,600 ሚ.ሜ የሚደርስ ሆኖ የዝናብ ስርጭቱ ከስድስት እስከ ሰባት ወራት ያህል ይቆያል፡፡

ክልሉ ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት ሽፋን ያለው ሲሆን ከጠቅላላ የቆዳ ስፋት ወስጥ 911,876 ሄ/ር ለእርሻ ምቹ የሆነ፣ 80,517 ሄ/ር በቀርከሀ፣ 161,605 ሄ/ር በሣር፣ 7,250 ሄ/ር ረግረጋማ፣ 15,216 ሄ/ር በውሃ፣ 422,630 ሄ/ር በቁጥቋጦ የተሸፈነ እና ቀሪው 114,048 ሄ/ር ድንጋያማ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ የክልሉ የተፈጥሮ ሀብት ሽፋን

| ተ.ቁ | የተፈጥሮ ሀብት | ሽፋን በመቶኛ |
|---|---|---|
| 1 | በተፈጥሮ ደን የተሸፈነ | 2 |
| 2 | በቀርቀሃ ደን የተሸፈነ | 7 |
| 3 | በሳር የተሸፈነ መሬት | 3 |
| 4 | ረግረጋማ መሬት | 0.15 |
| 5 | በውሃ የተሸፈነ መሬት | 0.2 |
| 6 | ድንጋያማ መሬት | 2 |
| 7 | በቁጥቋጦና በጥሻ የተሸፈነ መሬት | 28 |
| 8 | እንጨታማ መሬት | 43.5 |
| 9 | በመኖሪያቤትና ኀሮ የተሸፈነ | 1.65 |
| 10 | ለእርሻ የዋለ መሬት መጠን | 12.5 |

ምንጭ፡ የክልሉ አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አሰተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ

በክልሉ በብዛት ከሚመረቱ ሰብሎች መካከል በቆሎ፣ ማሽላ፣ ዳጉሳ፣ ሰሊጥ፣ ኑግ፣ ለውዝ ቀዳሚውን ሥፍራ ሲይዙ እንደ የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ሌሎች ሰብሎች የሚመረቱ ሲሆን በማኦ ኮሞ

ወረዳና በወንበራ ወረዳ የቡና ምርት በስፋት ይመረታል፡፡የክልሉ ዋና ዋና የዛፍ ዓይነቶች ሾላ፣ ዋንዛ፣ ዋርካ፣ ግራር፣ ብሳና፣ ዶቅማ፣ ቀርከሃ፣ የእጣን ዛፍ፣ ቀረሮ ወይራ፣ ዝግባ፣ ስሳ፣ አባሎ፣ ጥቁር እንጨት፣ ብርብራ፣ ቀውት ፣ከርች፣ አስታና የመሳሰሉት ሲሆኑ የዱር እንስሳት አይነቶች አንበሳ፣ ጐሽ፣ ድኩላ፣ ዝንጀሮ፣ ጦጣ፣ ጅብ፣ ሚዳቋ፣ ከርከሮ፣ የተለያዩ አእዋፋት እና ተሳቢ እንስሳት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

ክልሉ በአባይና በባሮ አኮቦ ወንዝ ተፋሰስ መካከል የሚገኝ በመሆኑ በውስጡ ለመስኖ ልማት የሚውሉ በርካታ ወንዞች ይገኛሉ፡፡ ለአነስተኛ መስኖ ልማት 1,687 ሄ/ር መሬት ማልማት የሚችሉ 28 ወንዞች መኖራቸውን በጥናት የተረጋገጠ ሲሆን ለመካከለኛና ከፍተኛ መስኖ ልማት መዋል ከሚችሉት ወንዞች ውስጥ በለስ 163,200 ሄ/ር፣ ዳቡስ 51,000 ሄ/ር፣ ግልገል-በለስ 88 ሄ/ር፣ ሰሊጋ 360 ሄ/ር በጠቅላላ 169,912 ሄ/ር መሬት በመስኖ መልማት ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ እየተከናወነ ያለው በክልሉ በጉባ ወረዳ ሲሆን 6,000 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም ይኖረዋል፡፡ ሌላው የክልሉን የተፈጥሮ ሀብት ባለፀጋነት ከሚያረጋግጡት መካከል እምነበረድ፣የፅንሠ-ወርቅ፣ የተለያዩ የኮንስትራክሽን ማዕድናት፣ ቤዝሜታል፣ የኢነርጅ ሀብት /ባዩጋዝ፣ የፀሐይና የነፋስ ኃይል/ በስፋት መኖራቸው ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ በክልሉ ሃይድሮ ፓወር ኤሌክትሪክ ሊያመነጩ የሚችሉ ወንዞች

| ተ.ቁ | የወንዙ ስም | ሊያመነጨውየሚችለው የሃይድሮፓዉር የኤሌክትሪክ በሜጋ ዋት |
|---|---|---|
| 1 | ሆሃ | 0.645 |
| 2 | ዳቡስ | 7.5 |
| 3 | ዱራ | 20 |
| 4 | ዲደር | 40 |
| 5 | መካከለኛው በለስ | 163 |
| 6 | ላይኛው በለስ | 200 |
| 7 | ታችኛው ዴዴሳ | 320 |
| 8 | ታላቁ የህዳሴ ግድብ (አባይ ወንዝ) | 6,000 |

ምንጭ፡ የክልሉ አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አሰተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ

## 2.2 አስተዳደራዊ ገፅታ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህዝብ እንደሌሎች ኢትዮጵያዊ ወገኖቹ በረቂቅ ህገ መንግስቱ ላይ ተወያይቶ ወኪሎችን በመምረጥና የህገሪቱን ህገ መንግስት በማጽደቅ ረገድ የራሱን አስተዋጽኦ ያበረከተ ሲሆን የክልሉ ህዝቦች የራሳቸውን ጉዳይ ራሳቸው የሚያስተዳድሩበት ሙሉ ስልጣን ተረጋግጦላቸው ከክልል ጀምሮ እስከ ቀበሌ መስተዳድር ድረስ የራሳቸውን አስተዳደር መስርተዋል፡፡ ክልሉ በ3 ዞኖች፣ በ19 ወረዳዎች፣ በአንድ ልዩ ወረዳና በአንድ ከተማ አስተዳደር እና በ475 የገጠርና ከተማ ቀበሌ አስተዳደሮች የተዋቀረ ነው፡፡ የክልሉ ርዕሰ ከተማም አሶሳ ስትሆን ከአዲስ አበባ በ 678 ኪ/ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡

የክልሉ ነባር ብሄረሰቦች በርታ (25.41%)፣ ጉሙዝ (20.88%) ሽናሻ (7.72%)፣ ማኦ (1.96%) እና ኮሞ (0.99%) ሲሆኑ የአማራ (21.69%)፣ የኦሮሞ (13.55%) እና ሌሎች (7.80%) ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በክልሉ ይኖራሉ፡፡

## ክፍል ሦስት፡ ባለፉት ሥርዓቶች የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ህዝቦች ይደርስባቸው የነበረ ጭቆናና ያካሄዱት ትግል

ባለፉት ስርዓቶች በሀገራችን ተንሰራፍተው በቆዩ አምባገነናዊና ፀረ-ዴሞክራሲ የፖለቲካ ሥርዓቶች የግፍ አገዛዝ የተነሳ የኢትዮጵያ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ታፍኖና ማንነታቸው ተረግጦ በመደብና ብሔር ጭቆና ሥር ወድቀው ለከፋ ድህነትና ኋላቀርነት ተዳርገው እንደነበረ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የልማትና የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚ ሳይሆኑ ከመቅረታቸው ባሻገር ለማንነታቸው እውቅና ተነፍጎ በመቆየቱ ባህላቸው፣ ቋንቋቸውና ታሪካቸው እንዳይታወቅና እንዳያድግ ተደርገዋል፡፡ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህዝቦችም እንደ ሌሎቹ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቹ በከፍተኛ ሁኔታ የስርዓቱ ተጎጂዎች የነበሩ ሲሆን በተለይም ነባር ብሔረሰቦቹ ይዞታቸውን በኃይልና በጦርነት እንዲለቁ ተደርጎ በአገራችን የተለያዩ ክፍሎች ተበታትነው እንዲኖሩ እና እየተገፉ በሀገሪቱ ጠረፋማ አካባቢዎች እንዲሰፍሩ ተገድደዋል፡፡ ስለሆነም ቋንቋቸው፣ ባህላቸውና ታሪካቸው ተገቢውን ክብርና እውቅና ተነፍጎት ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ያለፉት ጨቋኝ ሥርዓቶች ሁሉንም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የልማት፣የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች ጥያቄዎቻቸውን የረገጡና ያፈኑ መሆናቸው ሁሉም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ኃይሎች የሚገነዘቡት ሐቅ ቢሆንም፣ በተለይ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህዝቦች ያሳለፉት ጭቆና ግን እጅግ የከፋና የተደራረበ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

በእነዚህም ምክንያቶች የክልሉ ህዝቦች ለከፋ ድህነትና ኋላቀርነት የተዳረጉ ከመሆናቸው በላይ ማንነታቸው ተረግጦና በመልካቸው እና በቆዳ ቀለማቸው የተነሳ ሌላ ስም እየተሰጣቸው ተንቀውና በማንነታቸው ተሸማቅቀው ከነባር ይዞታቸውም ተገፍተው ለሰው ልጅ ኑሮ ምቹ ባልሆኑ ቆላማና ጠረፋማ አካባቢዎች ለመኖር የተገደዱ ሲሆን ያልተሰደዱት ደግሞ ያለማንነታቸው የሌሎችን ማንነት ተላብሰው በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ተበታትነው ለመኖር የተገደዱ ህዝቦች ነበሩ፡፡በመሆኑም እነዚህን ለበርካታ ዓመታት የተከማቹ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች እንዲሁም የብሄር ብሔረሰቦች የማንነት ጥያቄዎችን ለመፍታት ከሌሎቹ ወገኖች ጋር በመሆን በተደራጀና ባልተደራጀ መልኩ ለዘመናት ሲታገሉ ቆይተው በከፈሉት መስዋዕትነት ለዛሬው ህዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በትግላቸው ሊበቁ ችለዋል፡፡

የክልሉ ነባር ብሔረሰቦች ተወላጆች በተለያዩ የተቃውሞ አደረጃጀቶች እየተሳተፉ በግልና በተናጥል በሁሉም አካባቢዎች ሲደረግ የነበረው ትግልና መሰዋዕትነት እንደተጠበቀ ሆኖ በ1970ዎቹ እንቅስቃሴ የጀመረውና በዋናነት የበርታ ብሔረሰብ ተወላጆችን ያሰባሰበው የቤኒሻንጉል ህዝብ ነፃነት ንቅናቄ/ቤህነን/ በኢትዮጵያዊያን የዴሞክራሲ ኃይሎች ድጋፍ በ1981 ተመሥርቶ በ1982 የትጥቅ ትግል በመጀመር ለአፋኙና አምባገነኑ የደርግ ሥርዓት መደምሰስ የራሱን አስተዋጽኦ አድርጎ የሽግግር መንግሥት ከመሰረቱት የፖለቲካ ድርጅቶች አንዱ ለመሆን በቅቷል፡፡ በሌላ በኩል በዘመናት የህዝቦች ብሶት የተወለደው ህዝባዊ ትግል ሰምሮ የግንቦት 20/1983 ዓ.ም ድል ማግሥት በነፃ የመደራጀት መብታቸውን ተጠቅመው ከእነዚህ ህዝቦች ከየብሔረሰቡ በተውጣጡ ግንባር ቀደሞች አማካይነት የህዝባቸውን የልማት፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚነት ያረጋግጣል ብለው ያመኑበትን ፕሮግራምና ህገ ደንብ ቀርፀው፣ የጉሙዝ ህዝብ ነፃነት ንቅናቄ/ጎህነን/፣ የቦሮ ሺናሻ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ቦሮ ሺ.ህዴን/፣ የማኦ ህዝብ ዴሞክራሲዊ ድርጅት /ማህዴድ/

እና የኮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት /ኮህዴድ/ በሚሉ ስያሜዎች የሚጠሩ ብሔራዊ ድርጅቶች በ1984 ዓ.ም መሥርተው ሠላማዊና ዴሞክራሲያዊ ትግል አካሂደዋል፡፡

አምባገነኑ የደርግ ሥርዓት ከተገረሰሰ በኃላ የክልሉ ህዝቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ህገ-መንግሥታዊ ዋስትና በማግኘቱ፣ በብሔራዊ ማንነታቸው ተደራጅተው የራሳቸውን ክልላዊ መንግሥት በመመሥረት ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር፣ክልላቸውን የማልማትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማፋጠን ፣ የመሠረተ ልማት፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማት ለማረጋገጥ አዲስና ታሪካዊ ጉዞ የተያያዙበትና ህዝቦች በተጨባጭ ተጠቃሚ መሆን የጀመሩበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ የተመዘገቡት የልማትና መልካም አስተዳደር ስኬቶች የክልሉ ህዝቦች ለዘመናት ከነበሩበት ኋላቀርነትና የእድገት ደረጃ አንፃር ሲታይ ታሪካዊና እመርታዊ ለውጥ ነው ማለት ይቻላል፡፡

## ክፍል አራት፡- በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የተገኙ ውጤቶችና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ህዝቦች ተጠቃሚነት

### 4.1 በፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ የመንግስት አወቃቀርና በዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የተገኙ ውጤቶች

በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 39/1/2/3 መሠረት ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብና ህዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሠን እስከ መገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ መሆኑ፣ በቋንቋው የመናገር፣የመጻፍ፣ቋንቋውን የማሳደግና ባህሉንና ታሪኩን የመግለጽ፣ የማዳበር፣ የማስፋፋትና የመንከባከብ ሙሉ መብት እንዳለው እንዲሁም ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በአንቀጽ 50/1/2/4 ስለ ሥልጣን አካላት አወቃቀር በሚደነግገው ክፍል የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግስትና በክልሎች የተዋቀረ መሆኑ፣ የፌዴራሉ መንግስትና ክልሎች የሕግ አውጪነት፣ የሕግ አስፈጻሚነትና የዳኝነት ስልጣን እንደሚኖራቸውና ክልሎች በክልልነትና ክልሎች አስፈላጊ ሆነው በሚያገኙአቸው የአስተዳደር እርከኖች እንደሚዋቀሩ፣ ሕዝቡ በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች በቀጥታ ይሳተፍ ዘንድ ለዝቅተኛ እርከኖች በቂ ሥልጣን ይሰጣል ብሎ ይደነግጋል፡፡

በዚህ መሠረትም የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት በኢፌዴሪ ህገ መንግስት በተደነገገው መሠረት ተቋቁሞና ተደራጅቶ ራሱን ችሎ የክልሉ ህዝቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የሚወስኑበት ሁኔታ የተፈጠረ ሲሆን ያልተማከለ የአስተዳደር ሥርዓትን በክልሉ ውስጥ በመዘርጋት የክልሉ ህዝቦች አካባቢያቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በመሆኑም ያልተማከለ አስተዳደር ስርዓት በህገ መንግስቱ የተደነገገውን የህዝቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን ዴሞክራሲያዊ መብት በክልሉ ውስጥ እንዲረጋገጥ ወሳኝ ሚና ከመጫወትም በላይ የክልሉ ህዝቦች አከባቢያቸውን ለማልማት እንዲተጉ እድሉን በመክፈት ፍትሃዊ እድገት እንዲረጋገጥ እያስቻለ ይገኛል፡፡ በቀደምት ሥርዓቶች ማንነቱ፣ ቋንቋውና ባህሉ ታፍኖና ተረግጦ የኖረበት ዘመን አክትሞ የክልሉ ነባር ብሔረሰቦች ቋንቋቸውን በአደባባይ መግለጽና መጠቀም ከመቻላቸው በላይ በተለያዩ መድረኮችም ባህላቸውንና ታሪካቸውን በማስተዋወቅና በማስፋፋት በኩል ያገኙት ተጠቃሚነት በጣም የጐላ ነው፡፡

እነዚህ መብቶች በአግባቡ መከበራቸውን ለማረጋገጥና ለመከታተልም በክልሉ ውስጥ ህግ አውጭ፣ ህግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካላት ከክልል አንስቶ እስከታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ በአግባቡ ተቋቁመውና በሠው ኃይል ተደራጅተው የክልሉ ህዝቦች የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው እየወሠኑ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም የክልላችን ህዝቦች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ህጐች በማውጣትና በመፈፀም እንዲሁም ፍትህን በማግኘት ረገድ በከፍተኛ ሁኔታ በህገ መንግስቱ ትሩፋት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

## 4.2 የክልሉ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት

ከህገ መንግስቱ መሠረታዊ መርሆች አንዱ የህዝብ ሉአላዊነትን ማረጋገጥ ሲሆን በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ህዝቦች የአገሪቱ ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤቶች መሆናቸውን እና ሉዓላዊነታቸው የሚገለፀውም በህገ መንግስቱ መሠረት በሚመረጧቸው ተወካዮቻቸውና በራሱ በቀጥታ በሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካኝነት መሆኑን ሕገ-መንግስቱ ያስቀምጣል፡፡

በመሆኑም በህገ መንግስቱ መሠረት እስካሁን አራት አገር አቀፍና የክልል ምርጫዎች ህጋዊ መንገድን ተከትለው የተካሄዱ በመሆናቸው የክልሉ ብሔረሰቦች በአጠቃላይ የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤት መሆናቸውን በምርጫው ላይ በመሳተፍና ተወካያቸውን በመምረጥ የዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ አሁን በክልሉ ያለው መሪ ፓርቲ በይፋ ከመቋቋሙ በፊት የነበሩ 5ቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ክልሉን በመወከል በምርጫዎቹ በንቃት በመሳተፍ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት፣ በክልልና በወረዳ ምክርቤቶች ውስጥ ተሳትፎአቸው በጉልህ በማሳየትና የህዝብ ውክልና በማግኘት የህዝቡን ተጠቃሚነት ሊያረጋግጡ ችለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ያልተማከለ አስተዳደርን መሠረት በማድረግ የወረዳ አስተዳደሮች ተቋቁመው ተቋማቱ ለህዝቡ ቅርብ በመሆን ህግን የማስፈፀምና በዚሁም ህዝቡ ተጠቃሚ የሆነበት ሰፊ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ህዝቦች በክልል ም/ቤቶች፣ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤትና በፌዴሬሽን ም/ቤቶች ከሚኖራቸው የውክልና ተሳትፎ ባሻገር በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች በቀጥታ እንዲሳተፉ በማድረግ የወረዳና የቀበሌ አስተዳደሮች ተደራጅተው በአካባቢያቸው ጉዳይ ላይ በቀጥታ የሚወስኑበት ሁኔታ በማመቻቸት ህዝቡ በየደረጃው እንዲሳተፍና ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ ተፈጥሯል ፡፡

በሌላ በኩል የአንድ ዴሞክራሲያዊ ሀገር መገለጫ ከሆኑት አንዱ የሶስቱ የመንግስት አካላት ማለትም ህግ አውጭው፣ህግ ተርጓሚው እና ህግ አስፈፃሚው መኖር እና አንዱ ያለ አንዱ ጣልቃ ገብነት ስራቸውን በነፃነት መስራት መቻላቸው ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የክልሉ መንግስት እነዚህን የመንግስት አካላት በአግባቡ በማዋቀር እንዲሁም የብሔረሰብ ምክር ቤቶችን በማደራጀት ወደ ስራ ገብቷል፡፡ በህገ-መንግስቱ ድንጋጌዎች ላይ በመመርኮዝ የክልሉ ም/ቤት 99 መቀመጫዎች እንዲኖሩት ተደርጎ ተዋቅረዋል፡፡

ሠንጠረዥ 3፡ የክልል ም/ቤት አባላት

| የምርጫ ዘመን/ዓመት | ፆታ | | | ብሔረሰብ | | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | በርታ | ጉሙዝ | ሽናሻ | ማኦ | ኮሞ | |
| ከ1987-1992 | - | - | | - | - | - | - | - | መረጃ አልተገኘም |
| ከ1993-1997 | 88 | 12 | 100 | 41 | 35 | 11 | 2 | | 11 ሌሎች |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ከ1998-2002 | 89 | 10 | 99 | 35 | 35 | 10 | 2 | 2 | 16 ሌሎች |
| ከ2003-2007 | 85 | 14 | 99 | 39 | 35 | 11 | 2 | 2 | 10 ሌሎች |

ምንጭ፡ የክልሉ ም/ቤት ጽ/ቤት

ሠንጠረዥ 4፡ የ20 ወረዳና የአንድ ከተማ አስተዳደር ም/ቤት አባላት

| ምርጫ ዘመን/ዓመት | ፆታ | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | |
| ከ1985-1999 | - | - | - | መረጃ አልተገኘም |
| ከ2000-2005 | 1,861 | 368 | 2,229 | |
| ከ2006-2010 | 1,435 | 795 | 2,228 | |
| ድምር | 3,296 | 1,163 | 4,457 | |

ምንጭ፡ የክልሉ ም/ቤት ጽ/ቤት

ሕግ አውጪም በሕገ መንግስቱ የተሰጠውን ተግባራትና ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ ለማድረግ የሚያስችል አደረጃጀት፣አሰራርና በሰው ኃይል የማሟላት ስራ ተሰርቷል፡፡የህዝብ ምክር ቤቶች ለመልካም አሰተዳደር፣ ለህግ በላይነት መክበር፣ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት እድገት መፋጠን ወሳኝ የሆኑ ህጎችን ከማውጣት ጎን ለጎን የአስፈጻሚውን የሥራ አፈጸጸም የመከተታልና የመቆጣጠር ኃላፊነት ተሰጧቸዋል፡፡ ምክር ቤቱ ይህንን ሀላፊነት በአግባቡ ለመወጣት እንዲችል መደበኛው የምክር ቤት ተግባራት የሚያከናውኑ የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎች በማደራጀት የአስፈጻሚውን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴና የህግ ተረጓሚው አሰተዳደራዊ ስራዎች የመከታተልና የመቆጣጠር ተግባራት በማከወናቸው የህዝብ ተጠቃሚነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መዋተዋል፡፡

የዴሞክራሲ ተቋማት በተመለከተ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተጠሪ ጽ/ቤት፣ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ቅ/ጽ/ቤት፣ የሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ ዋናው ኦዲተር፣ የብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ፣ የህፃናት ፓርላማ ተቋቁመው በክልሉ በጅምር ላይ የሚገኘውን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ በማገዝ ላይ ይገኛሉ፡፡

በሌላ በኩል ክልሉ ከዚህ በፊት ያልነበረውን የራሱ የቴሌቪዢን አየር ሠዓትና አሶሳ ኤፍ.ኤም ሬዲዮ ባለቤት ሆኗል፡፡በዚህም የክልሉን ባህል፣ኢንቨስትመንትና ቱሪዝም አቅም እንዲሁም በየዘርፉ የሚከናወኑ የልማት ስራዎችን በጠንካራ የሚዲያ ሽፋን ማጀብ የሚቻልበትና የህብረተሰቡን የመረጃ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ በቀጣይ የክልሉን ህዳሴ ማብሰር የሚቻልበት ጉዞ ተጀምሯል፡፡

### 4.3 በፖለቲካ ዘርፍ የተገኙ ውጤቶችና የክልሉ ህዝቦች ተጠቃሚነት

በህገ መንግሥቱ ሙሉ ዋስትና ካገኙ መብቶች አንዱ የመደራጀት መብት ሲሆን ባለፉት ሃያ ሶስት ዓመታት በአገራችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ የመደራጀት መብት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል ለማለት ይቻላል፡፡ ከሽግግሩ መንግስት መቋቋም ማግስት አንስቶ በክልሉ ውስጥ ተደራጅተው ሠላማዊ ትግል ሲያካሂዱ የነበሩ ህዝባዊ የፖለቲካ ድርጅቶች የጉሙዝ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት፣የቦሮ-ሽናሻ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣ የማኦ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት፣የኮሞ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅትና ከሽግግሩ መንግስት መመስረት በፊት በ1970 እንቅስቃሴ የጀመረውና በ1982 የተመሠረተው በዋናነት የበርታ ብሄረሰብ ተወላጆችን ያሰባሰበው የቤኒሻንጉል ህዝብ ነፃነት ንቅናቄ (ቤህነን) በኋላም የኢትዮጵያ በርታ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት

(ኢ.በህዴድ) ናቸው፡፡ በእነዚህ ድርጅቶች ስር የተደራጁ ህዝቦች በርካታ የጋራ እሴቶችን ያዳበሩ በመሆናቸው በተናጠል ከሚያደርጉት የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥረቶች ባሻገር የበለጠ ውጤታማ ለመሆንና ህዝቡን የበለጠ ተጠቃሚ ለማድረግ ሲሉ በ1985 ዓ.ም የቤኒሻንጉልና የሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር በሚል ስያሜ የጋራ ግንባር መስርተው በዚሁ ግንባር የሚመራ ክልላዊ መንግስት በፍቃዳቸው በመመስረት የዘመናት የክልሉ ህዝቦች ጥያቄ የነበረውን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት እውን ማድረግ ችሏል፡፡

ይሁንና ከውጭ ኃይሎችና ከድርጅቶቹ የሚፈልቁ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከቶች ከነበረው ከፍተኛ የማስፈፀም አቅም ማነስ ጋር ተደምረው የተጀመሩትን የልማት እንቀስቃሴዎችን በተገቢው ፍጥነትና ጥራት ሊያስኬዱ አልቻሉም፡፡ በመሆኑም የውስጥ ድርጅት ሥራን ማቀጣጠልና የልማትና ዲሞክራሲ ግንባታን በህዝቡ ውስጥ ማስጀመር ሣይችሉ የሽግግሩ ዘመን ተጠናቀቀ፡፡ ከዚያም በኋላ ባሉት ጊዜያት በየድርጅቶቹ የነበሩ ችግሮችን የማጥራት ሥራ ከማካሄድ ጎን ለጎን አንድነቱን የበለጠ የማጠናከር አስፈላጊነት ላይ ስምምነት በመደረሱ በ1989 ዓ.ም የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር በሚል ስያሜ ድርጅቶቹ አንድነትን መስርተው የክልሉን ህዝብ የልማት፣ የሠላምና የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚ ለማድረግ ባደረጉት ጥረት ተጨባጭ ውጤት ሊመዘገብ ችሏል፡፡

ይሁን እንጂ በግንባሩ፣በአባል ድርጅቶችና በየደረጃው ባሉ የመንግስት መዋቅር የሚገኙ አመራሮች ቀደም ሲል ሲንከባለል ከመጣው ጠባብነት፣ፀረ-ዴሞክራሲያዊነት፣ቤተሰባዊነትና ቡድንተኝነት ችግሮች የተነሳ በሠላምና በልማት እንቅስቃሴው ላይ ችግር መፍጠሩ አልቀረም፡፡ ከዚህም የተነሳ በተለያዩ ወቅቶች እስከ 2002 ባሉት ጊዜያት በርካታ የሂስ ግለሂስ ግምገማዎች በአመራሮች፣በመሠረታዊ ድርጅቶች እና በግንባሩ ውስጥ በተለያዩ እርከኖች በሚገኙ አካላት መካከል የማጥራትና መስመር የማስያዝ ሥራዎች ተከናውነው ግንባሩ በበላይነት የክልሉን መንግስት የማስተዳደር ስራ አጠናክሮ ህዝቡ የልማትና ዲሞክራሲ ተጠቃሚ እንዲሆን ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በፖለቲካ ድርጅቶች ታሪክ ውስጥ ልዩ ቦታ የሚሰጠው እና ትልቅ እድገትና አዲስ ምዕራፍ የተጀመረበት የአራቱ ብሔራዊ ድርጅቶች ውህደት የተፈፀመበት ጥቅምት 12/ 2002 ዓ.ም ሲሆን በዚህም መሰረት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ቤጉህዴፓ) በሚል ስያሜ ወደ አንድ ፓርቲ የመዋሃድ ስርዓት ተፈፅሞ ፓርቲው ክልሉን እየመራ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ የክልሉ ነባር ብሔረሰቦች ብሔራዊ ድርጅቶችን አቋቁመው የህዝቡን ትግል በመምራት በግልም ሆነ በጋራ በመሠረቱት ግምባር አማካኝነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ የጋራ ግንባርና የክልላዊ መንግስትም አደራጅተው የህዝቡን የልማትና የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚ ለማድረግ ጥረት አድርገው ውጤትም አስመዝግበዋል፡፡

### 4.4 ቀልጣፋና ተደራሽነት ያለው የፍትህ ሥርዓት በመዘርጋት በኩል የተገኙ ውጤቶች

ከ1983 ዓ.ም በኋላ የሽግግር ወቅት ቻርተርን ተከትሎ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግሥት የሀገራችን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች በህገ-መንግሥቱ ባለቤቶች መሆናቸውን እውቅና በመስጠት የራሳቸው ህገ-መንግሥት እና የሉአላዊነታቸው መግለጫ ተደርጎ የተቀረጸ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ከህገ-መንግሥቱ መሠረታዊ መርሆዎች ውስጥ የህገ-መንግሥቱ የበላይነት በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 9 በዝርዝር የተደነገገ በመሆኑ ህገ-መንግሥቱም የሀገሪቱ የበላይ ህግ በመሆኑ ማንኛውም ህግ ልማዳዊ አሠራር እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ከዚህ ህገ-መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት እንደማይኖረው ከመደንገጉ ባሻገር ማናቸውም ዜጋ የመንግሥት አካላት የፖለቲካ

ድርጅቶች ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸውም ህገ-መንግሥቱን የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት እንዳለባቸው በአስገዳጅነት መደንገጉ፣ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከላይ በዝርዝር ለመግለጽ እንደተሞከረው ባለፈው ታሪካችን በነበሩ ሥርዓቶች የህግ-የበላይነት ያለመኖር ለአምባገንነት መስፈንና ለዴሞክራሲ እጦት ምክንያት የነበረ ይህንን ሁኔታ ሥር ነቀል በሆነ መንገድ መቀየር የግድ የሚል ነበር፡፡ በተጨማሪም የፌዴራላዊ የፖለቲካ ሥርዓት የሚከተል በመሆኑ የህገ-መንግሥቱን የበላይነት ልዩ የሚያደርገው ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሥልጣን ባለቤቶች መሆናቸውን መሠረት በማድረግ የመንግሥትን ስልጣን በፌዴራልና በክልል የሁለቱንም ሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት የወሰነበት፣ ፍ/ቤቶች የህግ የበላይነትን ለማስፈንና ለማረጋገጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ከመሆኑ የተነሣ የፌዴራልና የክልሎችን የዳኝነት የሥር ነገር ሥልጣን በማከፋፈል በግልጽ ያስቀመጠ ነው፡፡

ክልሉ ተረስቶ የቆየ እና በአዲስ መልክ የተቋቋመ በመሆኑ ህገ-መንግሥቱ ባጐናፀፈው መብት በመጠቀም የዳኝነት እና ሌሎች የፍትህ አካላት የራሱ ባህልና ማንነቱ በሚያውቁለት ብሔረሰቦች እና ተወላጆች በማሰልጠን የዳኝነት መዋቅሩን በመዘርጋት ፈርጀ ብዙ ሥራ በመስራት የክልሉን ኗሪ ወጭ ቆጣቢና ተደራሽ የዳኝነት አገልግሎት እንዲያገኝ ሰፊ ሥራ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

ከደርግ ስርዓት ውድቀት በኋላ በአገራችንም ሆነ በክልላችን የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መሠረቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 10 ላይ በተደነገገው እና የፌዴራልን ህገ-መንግሥት መሠረት በማድረግ ክልሎች በተሰጣቸው የህግ ማውጣት ሥልጣን በተሻሻለው የክልላችን ህገ-መንግሥት አንቀፅ 11 ላይ በግልጽ በመደንገጉ እነዚህም መብቶች ህገ-መንግሥታዊ ዋስትና አግኝተዋል፡፡

ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በማስጠበቅ ረገድ ህገ-መንግሥቱን መሠረት በማድረግ የፍትህ ሥርዓት በመዘርጋት ለነዚህ መሠረታዊ የሆኑ መብቶች ጥበቃ ትልቅ ቦታ በመስጠት ዘርዘርና ሰፋ ባለ ሁኔታ ሽፋን እንዲያገኙ በማድረግ ገለልተኛ የዳኝነት አካል በመፍጠር ለህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ ዘላቂነት በተግባር ሰፊ ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በክልላችን ለአብነት የሴቶች እና የህፃናት መብት ከማስጠበቅ አኳያ የእኩልነት መብት፣ የግል ህይወት የማስከበርና የመጠበቅ መብት፣ የሃይማኖት፣ የእምነትና የአመለካከት ነፃነት ወ.ዘ.ተ በማስጠበቅ ለተግባራዊነቱ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ሰፊ ሥራ በመሰራቱ አበራታች ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

ከ1983 ዓ.ም በኋላ በክልላችን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግሥት እና የተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግሥት መሠረታዊ መርሆዎች የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት መሠረት በማድረግ የመልካም አስተዳደር መስፈንና የክልሉ ህዝቦች ተጠቃሚነት ከጊዜ ጊዜ መሻሎችና በክልላችን በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሥር 3 የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤቶች እና በሥሩ የሚገኙ 20 ወረዳ ፍ/ቤቶች ተቋቁመው የዳኝነት አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን የክልሉን ህ/ሰብ እንግልትና ከብዙ ወጪ ለማዳን የፍ/ቤቶች ተደራሽነት ከክልሉ ወደ ማዕከል በሆኑ ዞኖች በየወረዳዎች በተመረጡ ቀበሌዎች በተዘዋዋሪ ችሎት የዳኝነት አገልግሎት በመስጠት በየጊዜው ከክልሉ ህዝብ ተጠቃሚነት አኳያ መሻሻሎች አየታዩ ነው፡፡ ለመሻሻሎቹም በዋናነት መንግሥት ትኩረት በመስጠት መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጦች እንዲጠኑ በማድረግ፣ የፍትህ ሠራዊት መደራጀት፣ የዜጎች ቻርተርን መሠረት ተደርጎ አገልግሎት በመስጠቱ ነው፡፡ በሁሉም ደረጃ ባሉ ፍ/ቤቶች የጥናት ሠነዱን መሠረት በማድረግ የዳኝነት አካሉ የሚጠበቅበትን ሥራ በተገቢው ፍጥነት፣ ጥራት እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ እያከናወነ ስለሆነ ለመልካም አስተዳደር መረጋገጥና ለክልሉ ህዝቦች ተጠቃሚነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

በተጨማሪም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍ/ቤቶችን ነፃነት ገለልተኝነት በጠበቀ መልኩ የፍትህ ሠራዊት መተግበሪያ ማንዋል በማዘጋጀት ዳኞችንና ሠራተኞችን አንድ ለአምስት በማደራጀት ለውጡን በየደረጃው ፍ/ቤቶች ተግባራዊ በማድረግ የክልሉ ህዝቦች ተጠቃሚነት ለማጎልበት በቁርጠኝነት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

የተፋጠነ ፍትህ ማግኘት ለተከራካሪ ወገኖች መብት በመሆኑ ቅልጥፍና የሌለው የፍትህ አካል የአገር ኢኮኖሚን በማሳደግና መብቶችን በማስጠበቅ ረገድ የጐላ ሚና ሊኖረው አይችልም፡፡ ይልቁንም ለፍትህ አካላት የሚቀርቡ ጉዳዮች ለረጅም ጊዜ በቀጠሮ የሚንከባለሉ፣ ባለጉዳዮችም ውጣ ውረድ የሚበዛባቸው ከሆነ በተፈለገው መጠን የልማት እንቅስቃሴ ለማፋጠን እንቅፋት እንደሚሆን ግልፅ ነው፡፡ ቀደም ሲል በነበረው ሥርዓት አንድ ጉዳይ ከሶ ለማስፈፀም እስከ 10 ዓመት ያህል እንደሚጓተትና ከመክሰስ ይልቅ መከሰስ ይሻላል ሲባል እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ ለውጡ ባስገኘው ውጤት በየደረጃው የተቋቋሙ ፍ/ቤቶች በሰው ኃይል እና በማቴሪያል በማደራጀትና መረጃ አያያዛቸውም ኮምፒውተራይዝድ በመደረጉ ሥራቸው ግልጽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ሆኗል፡፡ በአሁኑ ወቅት በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት መሠረት የክስ ጉዳዮች በአማካኝ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቅበት ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡

በተለይ ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ አብዛኛው ወደ ፍ/ቤት ከቀረቡት መዝገቦች ውስጥ 90 በመቶ ያህሉ ጉዳዮች ውሳኔ የተሰጣቸውን ሲሆን ይህም ፍ/ቤቱ የመወሰን አቅሙ ከዓመት ዓመት እየተሻሻለ መምጣቱን ያሳያል፡፡

በሌላ በኩል ባለፉት 14 ዓመት የማጥራት አቅም ከ94-129% የተመዘገበ ሲሆን ይህም የሚያሳየው በተወሰኑ ዓመት በጣም ጥቂት መዝገቦች ከአመት አመት የሚንከባለሉ መሆናቸውና አብዛኛዎቹ ግን በየዓመቱ የቀረቡ አዳዲስ መዝገቦች ሙሉ በሙሉ ውሳኔ እያገኙ መምጣታቸውን ያሳያል፡፡

ሌላው የፍርድ ቤቶች ቅልጥፍና መለኪያ የመጨናነቅ ሁኔታ ሲሆን ይህ መለኪያ ፍርድ ቤቱ አንድን መዝገብ ለመወሰን በአማካይ የሚፈጀውን ጊዜ የሚለካ ነው፡፡ ከላይ በተገለፀው መሠረት ፍርድ ቤቶች ምን ያህል መዝገብ እንደወሰኑ እንጂ እያንዳንዱ መዝገብ በአማካይ ምን ያህል ጊዜ እንደፈጀ አይገለጽም፡፡ ይህ የመለኪያ ዘዴ ለፍርድ ቤቱ የቀረቡ ጠቅላላ ጉዳዮች ውሳኔ ካገኙት ጋር የሚያነፃፅር ነው፡፡ በመሆኑም የፍርድ ቤቱን አጠቃላይ የሥራ ጫና የሚለካ ነው፡፡ በመሆኑም ከተሰበሰበው መረጃ ለመረዳት የሚቻለው አጠቃላይ ውጤቱ ከ1 በላይ የዘለለ ባለመሆኑ የዞሩ ጥቂት መዝገቦች መሆናቸውና መዝገቦች ለመወሰን የሚጠይቁት ጊዜ በአማካኝ 2 ወራት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

አሰተማማኝ የሆነ የፍትህ ስርአት እንዲኖሩ ለማስቻል የፍትህ አካላትን አሰራርና አደረጃጀት በሰው ኃይል ከማጠናከር ባሻገር ተጠያቂነትና ግልጸኝነት ያለው መዋቅራዊ አሰራር መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በክልሉ ውስጥ ባለፉት 23 ዓመታት የፍትህ ስርአት ማሻሻያ ፕሮግራምተቀርፆ ተግባራዊ ማድረግ የተቻለ ሲሆን በተለይም የፍትህ ተቋማት በአደራጃጀት፣ በአሰራርና በሠው ኃይል እንዲጠናከሩ በርካታ ስራዎች ተከናውኗል፡፡ በዚህም ረገድ አቃቢያነ ህግና ዳኞች በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ፣ በወለጋ፣ ባህር ዳርና በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች የረጅምና የአጭር ጊዜ ስልጠና እንዲያገኙ፣ ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉና ከክልል እሰከ ወረዳ እንዲመደቡ በማድርግ ህብረተሰቡ በቅርበት ፍትህ እንዲያገኝ ከፍተኛ ጥረት ተደረጓል፡፡

ነጻና ገለልተኛ የዳኝነት ስርአት መኖር ለአንድ ሀገር የህግ የበላይነት እና ሰብአዊ መብቶች መከበር ወሳኝ ቦታ የተሠጠው ጉዳይ በመሆኑ በክልላችን የዳኝነት ስርአትን በመዘርጋት የህግ የበላይነት ለማስፍን የዳኝነት አካሉ በህግ መንግስቱ ነጻ ፣ገለልተኛና ከማንም ጣልቃ ገብነት የጸዳ እንዲሆን

በመደረጉ የዜጎችን የፍትህ ጥማት ለማርካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከቱ ይገኛሉ ፡፡ የፍትህ ስርአቱ ተደራሽ ፣ቀልጣፍና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ከዚህ በፊት ይታይ የነበረውን የአገልጋይነት ችግር በመቅረፍ የዳኝነት አካሉ የህዝብ አገልጋይ በመሆን ህግና ህግን ብቻ መሠረት በማድረግ ተግባራቱን ለማከናወን እንዲያስችል የፍትህ ሥርአት ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት በተናጠል ከሚደረገው ጥረት ይልቅ ተቋሚዊ በሆነ ፣በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ በመስራቱ የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና ተደራሽነቱም ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎችና ለውጦች እያሳየ መጥቷል፡፡

የዳኝነት ስርአቱ የተሻለ የመፈጸም አቅም እንዲኖረው ለማስችል ተከታታይ የሆነ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች በየደረጃው እንዲያገኙ ተደረጓል፡፡ዘመናዊ የዳታ ቤዝ የመረጃ አያያዝ በመዘርጋትም ፍርድ ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጣቸው ግልጽና ቀልጣፋ እንዲሁም የዳኝነት አገልግሎት በመረጃ እና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን በመደረጉ አገልግሎቱ ወጪና ጊዜ ቆጠቢ እንዲሆን አስችሎታል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በ1986 ዓ/ም ሲመሰረት በ2 ክፍል፣ በ 9 ዳኞችና 57 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ሥራ የጀመረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በ33 የስራ ክፍሎች፣ በ136 የህግ ባለሙያዎችና 440 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ሥራውን እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሲመሰረት ምንም ዓይነት የሸሪዓ ችሎት ዳኛ ያልነበረ በአሁኑ ወቅት ግን 17 የናይባ/ የሸሪዓ ችሎት ዳኞች በመመደብ ስራውን እየሰራ ይገኛል፡፡

ሠንጠረዥ 5፡ የክልሉ የሕግ ባለሙያዎች በብሔረሰብ ስብጥር

| ብሔረሰብ | የህግ ባለሙያዎች | | | ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| በርታ | 27 | 8 | 35 | 2 | 2 | 4 |
| ጉሙዝ | 19 | 3 | 22 | 1 | 2 | 3 |
| ሽናሻ | 29 | 10 | 39 | - | - | - |
| ማኦ | 2 | - | 2 | 1 | - | 1 |
| ኮሞ | - | - | - | - | - | - |
| ሌሎች | 29 | 9 | 38 | 16 | 21 | 37 |
| ድምር | 106 | 30 | 136 | 20 | 25 | 45 |

ምንጭ፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት

የፍትህና ፀጥታ ሥራን ለማጠናከርና የአከባቢውን ሠላምና ፀጥታ በአስተማማኝ መልኩ ለማስጠበቅ የፖሊስና የሚሊሺያን ሀይሉን በማሰልጠንና በብቃት ህብረተሰቡ ተገቢውን ሰላምና ጸጥታ እንዲያገኝ ከመደረጉም በላይ ህገ መንግስቱና ሰብአዊ መብቶች በአግባቡ እንዲከበሩና እንዲጠበቁ የፀጥታና የፍትህ አካላቱ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች በተከታታይ ተሠጥቷቸዋል፡፡ የፀጥታ ኃይሉ በተለያዩ ወቅቶች የተሀድሶ ስልጠናዎችንም በተለያዩ ዙር እንዲያገኝ በመደረጉ ከፍተኛ የሆነ የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ ተደረጓል፡፡ በክልሉ የህግ የበላይነትና ፍትህን ለማረጋገጥ እንዲቻል እንዲሁም ወንጀልን ቀድሞ ለመከላከል የኮሚዩኒቲ ፖሊሲንግ ኦፊሰሮች በሁሉም የገጠር ቀበሌዎች ተደራሽ ለማድረግና ለማጠናከር ገና የሚቀረው ቢሆንም በተመደበበት በተለያዩ ቀበሌዎች አሰተማማኝ ሠላምና ፀጥታ ተጠናክሮ እንዲቀጥል በተደረገው ጥረት ህብረተሰቡ ተጠቃሚ ሆኗል፡፡

በክልሉ ውስጥ በሕዝብና በመንግስት ሀብት ላይ የሚፈጸመውን የሙስና ተግባር ለመከላከልና ኪራይ ሰብሳቢነትን ከምንጩ ለማድረቅ የሚያስችሉ ነጻና ገለልተኛ ተቋም ከመፍጠሩ ባሸገር በዘርፉ በአመለካከቱ ፣በስነ ምግበሩና በክህሎቱ የዳበረ ባለሙያ እና አመራር ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመር መጥቷል፡፡ በክልሉ ውስጥ የሙስና ወንጀሎች ከመከላከልና ወንጀሉ ተፈጽሞ ሲገኝ ከሶ የማሰመለስና የማሰቀጣት ስራዎች በመሰራቱ በርካታ የመንግስትና የህዝብ ሀብት ከመዝረፍና ከመመዝበር እንዲድን ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ ክልሉ ራሱን ችሎ ከተቋቋመበት ማግስት ጀምሮ የራሱ ዳኝነትና ህግ አስፈፃሚ አካልን በማደራጀት የክልሉ ህዝብ ራሱን በራሱ የሚዳኝበት ጠንካራ የዳኝነት የህግ አስፈፃሚነት ሥርዓት እውን ሆኗል፡፡

### 4.5 በመልካም አስተዳደር የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ህዝቦች ተጠቃሚነት

ከ1983 ዓ/ም ወዲህ መልካም አስተዳደርንና በየደረጃው የብዙሃኑን ሕዝብ ተጠቃሚነት ያረጋገጠ ዘላቂ ልማትን በማስፈን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ዓላማውና ግቡ ያደረገው የኢፌደሪ መንግሥት በተለይ ከ1997 ዓ/ም 3ኛው አገራዊ ምርጫ ማግሥት ጀምሮ በመልካም አስተዳደር ማስፈንና በሌሎችም የልማት ዘርፎች በርካታ ጥረቶችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተቀርጾ ከ1998 ዓ/ም ጀምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

በክልላችንም የመልካም አስተደዳደር ስራዎች ዘግይቶ ቢጀምርም በአጭር ጊዜ ውስጥ አበረታች ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡በየደረጃው የሚገኘው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ የሚሰጡት አገልግሎቶች በግልጸኝነት ላይ የተመሰርተ ፈጣንና በየደረጃው ህዝቡን ተጠቃሚ ያደረገ አገልግሎት እንዲሰፍን በማድርግ የተለያዩ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞች፣ ንዑስ ፕሮግራሞቸ እንዲሁም የለውጥ ፓኬጆች ተቀረጸው በሁሉም የአሰተዳደር እርከኖች እየተተገበረ ይገኛል፡፡

በገጠር ወረዳና ቀበሌ መልካም አስተዳደርን እውን ለማድረግ ከሕዝቡ እና ከመንግሥት ሠራተኛው የሚነሱ ቅሬታዎችን፣ ችግሮችንና የአፈጻጸም ክፍተቶችን በመለየትና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በመቀመር የገጠር አርሶ አደርና ወረዳ መልካም አስተዳደር ፓኬጁን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አደረጃጀቶች ተቋቁመው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡አመራሩና ሕዝቡ በዴሞክራሲያዊ መድረኮች በመወያየት፣ ማቀድ፣ መወሰን፣ ችግሮችን መፍታት ጀምሯል፡፡ ሕዝብ ያመነበትንና የወሰነውን ብቻ ሳይገደድ መሥራት መጀመሩና ያላመነበትን ጉዳይ ማዘግየት ወይም መተው መቻሉ፤ ሕዝቡ ሃሣቡን ያለፍርሃትና መሸማቀቅ አዎንታዊም ይሁን በአሉታዊ መንገድ መግለጽ መጀመሩ፣ እየገነባነው ላለው ስርዓት ጥሩ ጅምር ነዉ፡፡ በቀበሌዎች ሥራ አስኪያጆች ተቀጥረው ዘርፈ-ብዙ ሥራ እየሠሩና ሕዝቡ እየረካባቸው መሆኑ እና በወረዳዎች ቅሬታ ሰሚ አካላት ተቋቁመውና ሥልጠና ወስደው ወደ ሥራ በማስገባት ቅሬታዎችን እያስተናገዱ እና ምላሽ እንዲያገኝ እየተደረገ ይገኛል፡፡

የማስፈፀምና የመፈጸም አቅም ግንባታ ተቋማት በክልሉ የሚከናዋኑ የኢኮኖሚ ፣የማህበራዊና የዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ መጎልበት የማይተካ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በመሆኑም የክልሉ ህዝቦች ቀደም ሲል በነበሩት የአገዛዝ ስርአቶች እንደ ሠው የማይቆጠሩና የተረሱ ስለነበሩ የማስፈጸምና የመፈጸም አቅማቸው በዚያው ልክ ወደ ኋላ የቀረና ደካማ ነበር፡፡ይህንን ችግረ ለመቅረፍ ህግ መንግስቱ ካጎናፀፋቸው መብቶች አንዱና ዋነኛው የሆነው የራስን በራስ የማሰተዳደር መብትን በመጠቀም በክልሉ ውስጥ የስራ አመራር ተቋም ከመፍጠር አንስቶ የተለየዩ የክልሉ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲተዎች በማቋቋም የአመራር ፣የባለሙያና የተለያዩ ሕብረተሰብ ክፍሎች በአጭር፣ በመካከለኛና በረዥም፣ ጊዜ ሥልጠናዎች አቅማቸው እንዲጎለብት ሰፊ ጥረት ተደረጓል፡፡

በክልሉ የዴሞክራሲ ስርዓት እንዲጎለብትና ስር እንዲሰድ መልካም አስተዳደር እና የህግ የበላይነት በተሟላ መልኩ እንዲሰፌን በሕግ መንግስቱ የተረጋገጡ መብቶችና ነፃነቶች በተሟላ መልኩ እንዲከበሩ ለማድርግ የሚያስችሉ ህጎችን በማውጣትና ተቋማትን በማደራጀት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

የአስተዳደር ዘርፍ በርካታ ተቋማት የሚሰተፉበት ዴሞክራሲ መልካም አሰተዳደር እና የህግ የበላይነት የማስፌን እንዲሁም የዜጎች መብቶችና ነፃነቶች የማስከበር ዓለማ ያለው በመሆኑ በዚህ ዓለማ ዙሪያ በመንቀሳቀስ በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡

## ክፍል አምስት፡- በኢኮኖሚ ዘርፍ የተገኙ ውጤቶችና ለውጦች

### 5.1 የግብርናና ገጠር ልማት

የግብርና የልማት ዘርፍ ያለፉት ስርአቶች ሲከተሏቸው በነበረው የተሳሳቱ ፖሊሲዎችና ትኩረት ማነስ የተነሳ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሲዳከም ቆይቷል፡፡ ለዘመናት በቆየው ኋላቀርና ከእጅ ወደአፍ የሆነ፣ በቴክኖሎጂ ያልታገዘ አመራረትና የተፈጥሮ ጥገኝነት የክልሉ ህዝቦች ከዘርፉ ማግኘት የነበረባቸውን ጠቀሜታ ሳያገኙ ለድህነት ተዳርገዉ ቆይተዋል፡፡

የክልሉ ህዝብ ዋና የኢኮኖሚ መሠረት ግብርና ሲሆን 92.5 በመቶ የሚሆነው የህ/ሰብ ክፍል የተሠማራው በዚሁ ዘርፍ ላይ ነው፡፡ የክልሉ ጠረፋማ ወረዳዎች ከግብርናው በተጓዳኝ በባህላዊ መንገድ የወርቅ ቁፋሮ በማካሄድ ኑሮአቸውን ይደግፋሉ፡፡ ሆኖም አርሶ አደሩ ለዘመናት ይከተል የነበረው የግብርና ዘዴ ኃላቀር በሆነ የእርሻ መሣሪያና ቴክኖሎጂ ስለነበረ የክልሉ ምርትና ምርታማነት በተፈለገው መጠንና ደረጃ ሳያድግ ቆይቷል፡፡

የዘርፉን ኢኮኖሚ ለማሣደግ መንግሥት ካወጣው የግብርና መር ኢንዱስትሪ ፖሊሲ አንፃር የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ አርሶ አደሩ ከራሱ ፍጆታ አልፎ ለገበያ ሊያቀርብ የሚያስችለውን ምርት ለማምረት እንዲችል የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት በክልሉ ባሉት ወረዳዎችና ቀበሌዎች እየተተገበሩ ይገኛል፡፡

ከዚሁ አንፃር 104,869 አርሶ አደሮች በሚኒመም ፖኬጅ ተሣታፊ ሲሆኑ የክልሉ ቀደሞች ነዋሪዎችና የሴቶች ተሣትፎ በቅደም ተከተል 13.9 በመቶ እና 31.6 በመቶ ነው፡፡ ይህንኑን የግብርና ኤክስቴንሽንን በሥልጠናና በቴክኖሎጂ ለማገዝ እንዲቻል 269 የገበሬ ማሠልጠኛ ተቋማት /FTC/፣ 474 የልማት ጣቢያ ማዕከላት 20 የእንስሳት ጤና ክሊኒኮች፣ 324 የእንስሳት ጤና ኬላዎች፣ 1,926 የልማት ጣቢያ ሠራተኞች፣ 564 ረዳት የእንስሳት ጤና ሐኪሞችና 54 የጤና ቴክኒሺያኖች ለአርሶ አደሩ ዕገዛ እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ለመጣው የቴክኖሎጂ እገዛና የግብዓት አቅርቦት አንፃር የክልሉ የሰብል ምርታማነት በ2005/2006 በቆሎ 24.24 ኩ/ል፣ ማሽላ 21.73 ኩ/ል፣ ዳጉሳ 17.7 ኩ/ል እና ጤፍ 8.42 ኩ/ል በሄ/ር የተገኘ ሲሆን አጠቃላይ የክልሉ የሰብል ምርት ዕድገት 20.86 በመቶ ነው፡፡

የምርጥ ዘርና የማዳበሪያ አጠቃቀም በሚመለከት በቅደም ተከተል 0.23 ኪ.ግ እና 3.17 ኪ/ግ ሄ/ር ነው፡፡ ከሰብል ልማት በተጨማሪ ዋና የኢኮኖሚ ዘርፍ የአንስሳት ሀብቱ ሲሆን በክልሉ 489,369 የዳልጋ ከብቶች፣ 183,074 በጐች፣ 378,260 ፍየሎች፣ 76,506 የጋማ ከብቶች፣ 808,320 ዶሮዎችና 166,736 የንብ ቤተሰቦች ይገኛሉ፡፡

በእንስሳት ጤና አገልግሎት አንጻርም ከቅድመ ግንቦት 20/1983 በፊት ከጥቂት የወረዳ ከተሞች ዉጪ ያልነበሩ የእንስሳት ጤና ኬላዎች በአሁኑ ወቅት 312 ተቋማት አገልግሎት እየሰጡ ሲሆን የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሽፋኑ 88.87 በመቶ እና የእንስሳት ክትባት ሽፋን 70 በመቶ ደርሷል፡፡

አርሶ አደሩ ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ በዓመት እስከ 3 ጊዜ ማምረት የሚያስችሉ ለአነስተኛ፣ ለመካከለኛና ለከፍተኛ መስኖ ልማት መዋል ከሚችሉት ወንዞች ውስጥ በለስ 163,200 ሄ/ር፣ ዳቡስ 51,000 ሄ/ር ግልገል-በለስ 88 ሄ/ር ሡሊያ 360 ሄ/ር በጠቅላላው 169,912 ሄ/ር የማልማት አቅም ሲኖራቸው በአሁኑ ወቅት 15,690 ሄ/ር በመስኖ ለምቷል፡፡

በአጠቃላይ ከግንቦት 20/1983 በኃላ ክልላችንን ከድህነት ነፃ ለማዉጣት የሚያስችሉ የልማት ፖሊሲዎች በተለይም ግብርናና ገጠርን ማእከል ያደረገ ፖሊሲና ስትራቴጅዎች ተግባራዊ በመደረጋቸዉ በሀገሪቱ ያለዉ ፈጣን ቀጣይነት ያለዉ ፍትሀዊነቱ ከተረጋገጠዉ የኢኮኖሚ እድገት ተቋዳሽ ሆኖአል ፡፡ ግብርናን ማእከል ያደረገ የልማት ስትራቴጂ የተከተልንበት ዋነኛ አላማ ካፒታልን በቁጠባ በመጠቀም መሬትንና የሰው ጉልበትን በሰፊውና በላቀ ደረጃ ስራ ላይ በማዋል ኢኮኖሚውን በፍጥነት ለማሳደግ ስለሚያስችል ነው፡፡ ስትራቴጂው በምግብ እራስን መቻልን እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ግብአቶች የሚሆኑ የግብርና ምርቶችን በማስፋፋት በኢንዱስትሪና በግብርና መካከል ያለውን ትስስር ማጎልበትን እንደ አቅጣጫ ተይዞ ሲሆን በዚህም የሚያበረታታ ዉጤት ተመዝግቦአል፡፡ የክልሉ መንግስት ለተፈጥሮ ሀብት በሠጠዉ ትኩረት መሠረት የህዝብ ንቅናቄ በመፍጠር በ2006 ብቻ 27,510 ሄር የተፋሰስ ልማት ስራ ተሰርቷል፡፡

ሠንጠረዥ 6፡ የክልሉ መሬት አጠቃቀም ሁኔታ

| ተ.ቁ | የመሬት አጠቃቀም ሁኔታ | መጠን በሄ/ር |
|---|---|---|
| 1 | ለእርሻ ልማት ምቹ የሆነ መሬት | 2,316,939 |
| 2 | ለመስኖ ልማት ሊውል የሚችል መሬት | 194,607 |
| 3 | ለሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት ልማት ምቹ የሆነ መሬት | 1,405,063 |
| 4 | ለግብርና ኢንቨስትመንት አልሚ ባለሀብቶች እስካአሁን የተላለፈ መሬት (ለ327 ባለሀብቶች)<br>• በፌዴራል በውክልና ከተላለፊው ውስጥ ለ27 ባለሀብቶች 157,808 ሄ/ር<br>• በክልሉ መንግስት የተላለፈ ለ300 ባለሃብቶች 140,532 ሄ/ር | 298,340 |
| 5 | እስከአሁን በግል ባለሃብቶች ከተላለፈ መሬት ውስጥ የለማ መሬት | 42,116 |
| 6 | በአነስተኛ አርሶ አደር የለማ መሬት መጠን<br>• በዝናብ የለማ መሬት<br>• በመስኖ የለማ መሬት | 575,460<br>15,695 |
| 7 | የአልሚ ባለሀብቱ ተሳትፎ፡<br>• 50 ዲያስፖራ<br>• 29 የአካባቢው ነባር ቤሄረሰብ<br>• 248 የአገር ውስጥ ባለሃብቶች | |

| | | |
|---|---|---|
| 8 | በአነስተኛ አርሶ አደር፣ በመስኖና በባለሃብቶች የለማ መሬት ድምር | 633,271 |

ምንጭ፡ የክልሉ አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አሰተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ

## 5.2 ኢንቨስትመንት

ቀደም ሲል በክልሉ ምንም አይነት የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ያልነበረ ቢሆንም ከ1983 ዓ.ም ማግስት ጀምሮ መንግስት ለዘርፉ በሰጠው ልዩ ትኩረት በ1986 ዓ.ም ለ 8,075 ዜጎች የሥራ ዕድል የሚፈጥር ብር 34,300,800.00 ካፒታል ያስመዘገበ አንድ ፕሮጀክት የተመዘገበ ሲሆን እስከ 2005 ዓ.ም ከተመዘገበው ጭምር በአሁኑ ሠዓት በክልሉ በአጠቃላይ የተመዘገቡ ፕሮጀክቶች ብዛት 1,171 ያስመዘገቡት ካፒታል ብር 5,639,240,614 የተፈጠረ የሥራ ዕድል ደግሞ 157,505 ደርሷል፡፡ይህም የክልሉ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ ዕድገት እያሳየ እንደሚገኝ አመላካች ቢሆንም በተለይም እንደ ወርቅና ዕምነበረድ በመሳሰሉ ማዕድናት፣በግብርና ኢንቨስትመንትና በቱሪዝም ልማት ክልሉ ካለው ዕምቅ የኢንቨስትመንት አቅም አንፃር በዘርፉ ገና ብዙ ሊሠራበት እንደሚገባም ጭምር የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ መልኩ በእርሻ ኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሀብቶች የቅርብ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የወሰዱትን መሬት አሟጠው እንዲያለሙ እና ከብልሹ አሰራር እንዲፀዱ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ሠንጠረዥ 7፡ የክልሉ የኢንቨስትመንት አማራጮች

| ተ.ቁ | ዘርፍ |
|---|---|
| 1 | ግብርና<br>• የአገዳ ሰብል፣ የብዕር ሰብል፣ የቅባት እህሎች፣ የጥራጥሬ ሰብሎች፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ የጭረት ሰብል፣ ቡና፣ ቅመማቅመም፣ የስራስር ሰብሎች እና የሸንኮራ አገዳ<br>• የምግብ ማቀነባበር<br>• የእንስሳት ሀብት ልማት<br>✓ የአሳ እርባታ<br>✓ የከብት እርባታና ማደለብ<br>✓ የበግና ፍየል እርባታ<br>✓ ንብ ማነብና ማርባት<br>✓ የዶሮ እርባታ |
| 2 | አግሮ ፕሮሰሲንግ<br>• ቡና መቁላት መፍጨትና ማሸግ<br>• ወተትና የወተት ተዋጸዎች ማቀነባበር<br>• ቅመማቅመም ማቀነባበርና ማሸግ<br>• አትክልትን ፍራፍሬ ማቀነባበር<br>• ዱቄት ማቀነባበር<br>• ማር ማቀነባበር<br>• የእንስሳት መኖ ማቀነባበር<br>• የአኩሪ አተር ወተት ማቀነባበር<br>• ስጋ ማቀነባበርና ማሸግ |

| | |
|---|---|
| | • የኦቾሎኒ ቅቤ ማዘጋጀት |
| 3 | ማኑፋክቸሪነግ<br>• የወረቀት ማምረቻ ፋብሪካ<br>• ካርቶን ማምረቻ ፋብሪካ<br>• ናጵኪን ማምረቻ ፋብሪካ<br>• ፖስታና የወረቀት ቦርሳ ማምረቻ ፋብሪካ<br>• የደብተር ማምረቻ ፋብሪካ<br>• የህትመት ፋብሪካ<br>• የስኳር ፋብሪካ<br>• የእምነበረድ ውጤቶች ማምረቻ ፋብሪካ |
| 4 | ማዕድን ሀብት<br>• ለኢንዱስትሪ አግግሎት የሚውሉ ማዕድናት<br>✓ የግራናይት ክምችት<br>✓ የቶርማላይን ክምችት<br>✓ የግራፋይት ክምችት<br>✓ የካዎልን ክምችት<br><br>• ብረት ነክ ማዕድናት<br>✓ ወርቅ (ጽንሰ ወርቅና ደለል ወርቅ)<br>✓ የመዳብ ክምችትየክሮማይት ክምችት<br>✓ የብረት ክምችት<br>✓ የሞልብዳናይት ክምችት<br>✓ የፓራይት ክምችት<br>• ብረታ ብረት ያልሆኑ ማዕድናት<br>✓ ሰማያዊ እምነበረድ<br>✓ ነጭ እምነበረድ<br>✓ ጠጠር<br>✓ ሸክላ<br>✓ ጥቁር ድንጋይ<br>✓ ኖራ<br>✓ ጅብሰም<br>✓ የከበሩ ድንጋዮች |

ምንጭ፡ የክልሉ አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አሰተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ

## 5.3 ገቢ አሰባሰብ

በ1983 እና በ1984 ዓ.ም በክልላችን የተሰበሰበ የገቢ መረጃ ያልተገኘ ቢሆንም በጊዜው ከደመወዝ ገቢ ግብር ያለፈ ትርጉም ያለው ገቢ ያልነበረ መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ሆኖም በ1986 ዓ.ም ብር 3 ሚሊዮን ገቢ የተሰበሰበ ሲሆን በ2005 ዓ.ም 250 ሚሊየን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 269,536,683.80 ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በ2006 የበጀት ዓመት ለመሰብሰብ የታቀደው ብር

300 ሚሊዮን ሲሆን ብር 323,751,594.15 የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙም 107.92% ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ገቢ የመሰብሰብ አቅማችን ተጠናክሮ ከቀጠለ ወደፊት የክልሉን ልማት በማፋጠን ድርሻው የላቀ እንደሚሆን የሚያሳይ ነው፡፡

### 5.4 የመንደር ማሰባሰብ ሥራችን

በክልሉ ተበታትኖ የሚኖረውን አርሶ አደር ውሃን ማዕከል ባደረገ በአማካይ ቦታ በማሰባሰብ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ተጠቃሚ ለማድረግ በታቀደው መሰረት የ5 ዓመቱ ተደራሽ ግብ በ45 ማዕከላት ለማሰባሰብ የታቀደ ሲሆን ከ2003-2006 ዓ/ም በተካሄደ በመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራም የታቀፉ ማዕከላት ብዛት 221 ናቸው፡፡

በአሳለፍናቸው ተከታታይ የመንደር ማሰባሰብ አመታት በተደረገዉ የመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራም በጥናት ተለይተዉና በዕቅድ ተይዘዉ የተከናወኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ብዛት 664 የተቋማት ግንባታ ዉስጥ 484 የተቋማት ግንባታ የተጠናቀቀ ሲሆን ቀሪዎቹ በግንባታ ሂደት፣ በዉል መቋረጥና በበጀት እጥረት ምክንያት ደረጃ በደረጃ ገና የሚገነቡ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ከ2003-2006 ዓ/ም በተደረገዉ የመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራም 40,465 አባ/እማወራዎችን በተመረጡ 221 ማዕከላት ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸማችን ከእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ከተያዘዉ 45,000 አባ/እማወራ የማሰባሰብ ዕቅድ ጋር ሲነጻጸር 90 በመቶ ነዉ፡፡

ሠንጠረዥ 8፡ በመንደር ማሰባሰብ ማዕከላት የተገነቡ ተቋማት /ከ2003ዓ- 2006 ዓ.ም/

| ተ.ቁ | የተቋሙ ስም | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | የእንስሳት ጤና ኬላ | 157 | 136 ተጠናቅቀው ወደ አገልገሎት ገብቷል፡፡ |
| 2 | የአርሶ አደር ማሠልጠኛ | 129 | 108 ተጠናቅቀው ወደ አገልገሎት ገብቷል፡፡ |
| 3 | የሰው ጤና ኬላ | 96 | 86 ተጠናቅቀው ወደ አገልገሎት ገብቷል፡፡ |
| 4 | አንደኛ ደረጃ ት/ቤት | 102 | 74 ተጠናቅቀው ወደ አገልገሎት ገብቷል፡፡ |
| | ድምር | 484 | 404 |

ምንጭ፡የክልሉ ምግብ ዋስትናና ሕዝብ አሠፋፈር አደጋ መከላከል ዝግጁነት ጽ/ቤት

## 5.5 የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት

የክልሉ መንግሥት ለጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትና የሥራ ፈላጊዎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ ድህነትን ለመቀነስ ተቋማቱን ማጠናከር ወሣኝ በመሆኑ የዘርፉን መዋቅር በመዘርጋት የሰው ሀይል ከሞላ ጐደል በሚሟላትና ለልማቱ ሥራም ትኩረት በመስጠት የመደበኛና የካፒታል በጀት ተመደቦ እየተሰራ ይገኛል፡፡

በዚሁም ጥረት እስካሁን በክልሉ የሚገኙ ወረዳና ከተሞች በማኑፋክቸሪንግ፣ በኮንስትራክሽን፣ በከተማ ግብርና በአገልግሎትና በንግድ ዘርፎች በአጠቃላይ ለ913 የሚሆኑ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማደራጀት ለ18,173 ዜጐች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድልተፈጥሯል፡፡ መንግሥት ማቅረብ ካለበት መንግሥታዊ ድጋፍ አኳያ የብድር አቅርቦት የማምረቻና መሸጫ ቦታዎች፣ የገበያ ትስስር፣ የስልጠና፣ የኢንተርፕራይዞች የደረጃ ሽግግር ሥራዎች በተጨባጭ እየተሰራ ካሉት ሥራዎች መካከል ተጠቃሽ ነው፡፡

ዘርፉ ለዜጐች የሥራ እድል የሚፈጥርበትና የልማታዊ ባለሀብቶች መፍለቂያ መሆኑ በገሀድ የታየ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በክልሉ ተደራጅተው ተጠቃሚ በመሆን የተሸጋገሩና በርካታ ሀብት በማፍራት ለሌሎች ዜጐች አርአያ ሊሆኑ የቻሉ ይገኛሉ፡፡

በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሽግግር መመሪያ መሠረትም በአሶሳ ከተማ ከተደራጁት ኢንተርፕራይዞች ውስጥ ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ 2፣ ከኮንስትራክሽን ዘርፍ 1፣ በድምሩ 3 ኢንተርፕራይዞች ከ1.5 ሚሊዮን ብር በላይ በማስመዝገብ ከመብቃት ወደ ታዳጊ መካከለኛ ተሸጋግረዋል፡፡

በከተማ ልማት ዘርፍም በክልሉ የተጀመሩ የኮብልስቶን ነጠፋ ሥራ በካማሺ ዞንና በግልገል በለስ ከተማ የተጀመሩ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ለ356 ዜጐች ጊዜያዊ የሥራ እድል ተፈጥሯል፡፡

ለዚህ ዘርፍ በቀጣይ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ለበርካታ የክልላችን ዜጎች የስራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ የምንቀሳቀስ ሲሆን የማምረቻና መሸጫ ማዕከላት የብድር አቅርቦትን ተደራሽነት በማሳደግ የጥ/አ/ተቋማት እንቀሣቃሾችን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚሰራ ይሆናል፡፡

ሠንጠረዥ 9፡- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሥራዎች

| ተ.ቁ | የተሠሩ ሥራዎች | 2003-2006 | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | ነባር ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት መደገፍና ማጠናከር | 2,936ነባር ኢንተርፕራይዞች በስልጠናና በገበያ ትስስር በኩል ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ | |
| 2 | የተፈጠረ አዲስ የሥራ ዕድል | 14,680 ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡ | |
| 3 | የሴቶች ተሳትፎ | 38.5% | |
| 4 | የተሰጠ ብድር | 7.5 ሚሊዮን ብር | |
| 5 | የቁጠባ መጠን | 1.6 ሚሊዮን ብር | |
| 6 | የገበያ ትስስር በገንዘብ | 110,265,000 ብር | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7 | መሥሪያና መሸጫ ቦታ | 70,200 ካሬ ቦታ ተሰጥቷል፡፡ | |

ምንጭ፡ የክልሉ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጄንሲ

## ክፍል ስድስት፡- በመሠረተ ልማት ዘርፍ የተገኙ ውጤቶችና ለውጦች

### 6.1 መንገድ

ከግንቦት 20/1983 ዓ.ም በፊት በክልላችን ውስጥ የነበረው የመንገድ ሽፋን ከ420 ኪ/ሜ ያልዘለለ የነበረ ሲሆን ይህ አሀዝ በአሁኑ ወቅት ልማታዊ መንግስታችን ለዘርፉ በሰጠው ልዩ ትኩረት የክልሉ የመንገድ ሽፋን 1,530 ኪ/ሜ ሊደርስ ችሏል፡፡

ከዚህም ውስጥ 945 ኪ/ሜ በክልሉ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን ስር የሚተዳደር እና 585 ኪ/ሜ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የሚተዳደር ነው፡፡

የመንገዱን ደረጃ በተመለከተ አስፋልት 176 ኪ/ሜ እና ጠጠር 1,354 ኪ/ሜ ሲሆን የመንገዱ ፋይዳ ደግሞ ከአዲስ አበባ-አሶሳ እና ከአሶሳ-አዲስ አበባ በአማካይ ከ2-3 ቀናት ይፈጅ የነበረው ጉዞ በአሁኑ ወቅት ወደ 1 ቀን እስከ 1 ቀን ተኩል ዝቅ ማለቱንና ያለ እንግልትና መጉላላት ምቹ የትራንስፖርት አገልግሎት ማግኘት ተችሏል፡፡

የክልሉ መንግስት ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ ሁሉንም ወረዳዎች ከዞን ማዕከላት እና ከክልል ርዕሰ ከተማ የሚያገናኝ መንገድ ባለቤት እንዲሆን ያደረገ ሲሆን በቀጣይም በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ቀበሌዎች ከዋና መንገድ ጋር የማገናኘቱ ስራ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ የሚከናወን ይሆናል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በሕብረተሰቡ ጉልበት የተገነቡና በበጋ ወራት አገልግሎት የሚሰጡ 4,692 ኪ/ሜ የማህበረሰብ መንገዶች ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ግንባታቸው ተጠናቆ ለትራፊክ ክፍት ሊሆኑ የሚችሉ በክልሉ ዞኖችና ማኦ-ኮሞ ልዩ ወረዳን ጨምሮ በ18 ወረዳዎች እየተገነባ ያለው 480 ኪ/ሜ የዩራፕ መንገዶች በመገንባት ላይ የሚገኙ እና ወረዳን ከቀበሌ እንዲሁም ቀበሌን እርስ በርሱ እና ክረምት ከበጋ አገልግሎት ከሚሰጠው ከዋና መንገድ ጋር የማያያዝ መርሃ-ግብር ነው፡

ሠንጠረዥ 10፡ የመንገድ ሽፋን በኪሎ ሜትር

| ተ.ቁ | አመልካች | ከ1983 ዓ.ም በፊት | እስከ 2006 ዓ.ም | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አጠቃላይ የመንገድ ርዝመት/በኪሎ ሜ/ር/ | 316 | 1,547 | |
| 2 | የመንገድ ጥግግት | 6.27 | 30.71 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | በጥሩ ይዞታ ላይ የሚገኝ መንገድ በመቶኛ | - | 95 | |
| 4 | የገጠር ቀበሌዎች የሚያገናኝ የገጠር መንገድ ግንባታ /በኪ.ሜ/ | - | 4,122 | |

ምንጭ፡የክልሉ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን

## 6.2 ቴሌኮሙኒኬሽን

የክልላችንን እድገት ለማፋጠን ከፍተኛ ጠቀሜታ ካላቸው የመሰረተ ልማት አውታሮች መካከል የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ዋነኛው ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ከ1983 ዓ.ም በፊት የነበረው የመደበኛ ስልክ አገልግሎት ከአሶሳ ከተማ ውጭ እዚህ ግባ የማይባልና የክልሉን ህዝብ በአጠቃላይ ተጠቃሚ ያላደረገ የነበረ ሲሆን መረጃው መያዝ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በ2006 ዓ.ም በክልሉ የመደበኛ ስልክ አገልግሎት በ11 ወረዳዎች ላይ ተተክሎ 5,458 ደንበኞች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል ፡፡
የዋየርለስ ስልክን በተመለከተ እስከ 1983 ምንም ያልነበረ ሲሆን ከ1983 ወዲህ አገልግሎቱ መሰጠት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ ብቻ በክልሉ በሚገኙ 20 ወረዳዎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር ተደራሽ በማድረግ በክልሉ ከሚገኙ 475 ቀበሌዎች መካከል 458 (96.4%) ቀበሌዎች የዋየርለስ ስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ የሞባይል ስልክን በተመለከተ ቀደም ሲል በክልሉ ብቻ ሳይሆን በሀገር አቀፍ ደረጃም ያልነበረ ሲሆን በአሁን ወቅት በክልሉ በሚገኙ በሁሉም ወረዳዎችና በበርካታ ቀበሌዎች ላይ ተደራሽ እንዲደረግ ተደርጓል፡፡
የትምህርት ስርጭት በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ከማገዝ አኳያ በተለያዩ ወረዳዎች በሚገኙ 45 ት/ቤቶች ላይ የፕላዝማ ስርጭት አገልግሎት ተደራሽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በክልሉ በሚገኙ 20 ወረዳዎች የወረዳኔት ስርጭት በቪሳትና በኤ ዲ ኤስ ኤል በመጠቀም ተደራሽ ማድረግ ተችሏል፡፡

## 6.3 የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት

የሀገራችን የውሃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲ ዋነኛ ግብ ውሃ ፍትሃዊ እና ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ እንዲሁም በአግባቡ በማልማት ለማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ማድረግ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በ1983 ዓ.ም የክልሉ የመጠጥ ውሃ ሽፋን ከ12.39 በመቶ ያልበለጠ የነበረ ሲሆን የክልላችንን ህብረተሰብ የንፁህ መጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ መንግስት በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን የቆየ ሲሆን በ2006 ዓ.ም የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋኑ በከተማ 72 በመቶ እና በገጠር 82.3 በመቶ በጥቅሉ የክልሉ የመጠጥ ውሃ ሽፋን 81.3 ከመቶ ደርሷል፡፡
የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት ለማሣደግ በተደረገው ጥረት እስከ 2006ዓ/ም መጨረሻ ድረስ 1,589 የእጅ ውሃ ጉድጓድ፣ 1,014 መለስተኛ ጥልቅ ጉድጓድ፣ 226 የጐለበተ ምንጭ እና 36 የጥልቅ ጉድጓድ በድምሩ 2,865 ተገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

ሠንጠረዥ 11፡ የንፁህ መጠጥ የውሃ ሽፋን

| ተ.ቁ | አመልካች | በ1983 ዓ.ም | በ2006 ዓ.ም | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አጠቃላይ የክልሉ መጠጥ ውኃ ሽፋን በመቶኛ | 12.39 | 79 | |
| 2 | የንፁህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በከተማ በመቶኛ | - | 71 | |
| 3 | የንፁህ መጠጥ ውኃ ሽፋን በገጠር በመቶኛ | - | 80 | |

ምንጭ፡ የክልሉ ውሃ ማዕድንና አነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ

## 6.4 ባንክ

የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ እድገት አመላካች ከሆኑት ተቋማት መካከል የባንኮች እና ፋይናንስ አገልግሎት ሰፊ ተቋማት መኖርና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የፋይናንስ አቅርቦት በወቅቱ እና በተፈለገው ጊዜ ማግኘት መቻል ነው፡፡ በመሆኑም ከ1983 ዓ.ም በፊት አንድ የኢትዮጵ ንግድ ባንክ አሶሳ ቅርንጫፍ ብቻ በክልሉ የነበረ ሲሆን በ2006 ዓ.ም በግልገል በለስ፣ጉባ፣ቡለን፣ወንበራ፣ባንባሲ፣ካማሽ፣አሶሳ ሁለተኛ ተጨማሪ ኢንዚ ቅርንጫፍ በድምሩ 8 የኢትዮጵ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች፣ አንድ የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ እና አንድ የመድን ድርጅት በድምሩ 10 የመንግስት ባንኮችና የመድን ድርጅት ይገኛሉ፡፡

ከግል ባንኮች መካከል አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ፣ዓባይ ኢንተርናሽናል ባንክ፣አሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ፣ ወጋገን ኢንተርናሽናል ባንክ፣ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ እና ህብረት ኢንተርናሽናል ባንክ በድምሩ 6 የግል ባንኮች በአጠቃላይ በክልላችን ይገኛሉ፡፡ በ1983 ዓ.ም በክልሉ አንድ ባንክ ብቻ የነበረው በ2006 ዓ.ም አስራ አምስት ባንኮች እና አንድ የመድን ድርጅት መኖራቸው የክልሉን የንግድና ኢንቨስትመንት እንዲሁም የኢኮኖሚና ፋይናንስ እንቅስቃሴ መሻሻል ብቻ ሳይሆን የወደፊት የክልሉን ልማትና እድገት ብሩህ ተስፋነት የሚያሳይ ነው፡፡

## 6.5 ብድርና ቁጠባ ተቋም

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላ ብድርና ቁጠባ ተቋም በ1993/94 በጀት ዓመት ሲቋቋም በብር 300,000 መነሻ ካፒታል ሲሆን በ2006 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ከ40 ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል ደርሷል፡፡ ከደንበኞች የተሰበሰበ ቁጠባን እና ቦንድን በሚመለከት በ2002 ዓ.ም ከነበረበት 20.7 ሚሊዮን ወደ 55.3 ሚሊዮን ብር ደርሷል፡፡ በ2002 በጀት ዓመት አጠቃላይ የደንበኞች ብዛት 30,378 የነበሩ ሲሆን በ2006 በጀት ዓመት ለ40,823 ደንበኞች ብድር ተሰጥቷል፡፡ በ2002 በጀት ዓመት የተሰራጨ ብድር ብር 25,704,492.20 የነበረ ሲሆን በ2006 በጀት ዓመት የተሰራጨ ብድር ወደ ብር 82,975,507 ከፍ ብሏል፡፡ የብድር አመላለስ ምጣኔውን በተመለከተ በ2002 ከነበረበት 45 ከመቶ በ2006 በጀት ዓመት ወደ 70 ከመቶ ለማድረስ ተችለዋል፡፡ አጠቃላይ የተሰራጨ ብድር ወደ 117 ሚሊዮን ብር ሊደርስ ችሏል፡፡

## 6.6 መብራት

መብራት የአንድ ሀገር የኢኮኖሚ እንቀሳቃሽ ሞተር ነው፡፡ በመሆኑም በርካታ የክልላችን ከተሞች እና ቀበሌዎች የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆኗል፡፡ ከ1983 በፊት በአሶሳ ከተማ ብቻ (ያውም የአራት

ሰዓት አገልግሎት ብቻ) ተወስኖ የነበረው የመብራት አገልግሎት በ2006 ዓ.ም ከ,ያሶ ከተማ በስተቀር 104 ,ያህል የወረዳ ከተሞችና ቀበሌዎች የ24 ሰዓት መብራት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ የወምበራ ወረዳ ደብረ ዘይት ከተማ የዲዝል ጄነሬተር መብራት ተጠቃሚ ሲሆን ባሁኑ ወቅት የ24 ሰዓት መብራት መስመር ዝርጋት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

## ክፍል ሰባት፡- በማህበራዊ ዘርፍ የተገኙ ወጤቶችና ለውጦች

### 7.1 ትምህርት

ከደርግ ውድቀት በፊት የነበረው የክልላችንን የዘመናዊ ትምህርት ታሪክ በዋና ዋና ከተሞች ላይ ብቻ የታጠረ ስለነበር የክልላችን ነባር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ለዘመናት ከዘመናዊ ትምህርት ተገልለው ኖረዋል። የትምህርት ስርዓቱ ኢ-ፍትሐዊ ከመሆኑም በላይ በሽፋንም እጅግ አነስተኛ የነበረና ከፍተኛ የጥራት ችግር የተጠናወተው ነበር። በእነዚያ የጭቆናና የዓፈና ዘመናት የክልላችንን አርሶ አደሮች የዘመናዊ ዕውቀት ባለቤት ማድረግ ስላልተቻለ ህይወታቸው በቀጣይነት ከመሻሻል ይልቅ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ እንዲመጣ ከፍተኛ ድርሻ ነበረው።

የአንድን ክልል ዘላቂ ዕድገት ማረጋገጥ የሚቻለው በክልሉ የተነደፉትን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በጥልቀት ተገንዝቦ በብቃት መፈፀምና ማስፈፀም የሚችል ብቃት ያለው የሰለጠነ የሰው ሃይል በበቂ ሁኔታ ማሰናዳት ሲቻል በመሆኑ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ የክልላችን መንግስት ባሳለፍናቸው ተከታታይ 23 ዓመታት ለትምህርት ዘርፍ የሰጠው ትኩረት እጅግ ከፍተኛ ነው። በበቂ ዕውቀት የታጠቀ ዜጋ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ከመፈፀምና ከማስፈፀም በተጨማሪ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቱንና ግዴታውን በአግባቡ በመወጣት በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደትም ገንቢ ሚና ለመጫወት የሚያስችለው ዕድል ሰፊ ነው።

በመሆኑም ሁሉም የክልላችን ህዝቦች ትምህርት በቅርብ ርቀት የሚያገኙበት ፍትሐዊ ስርዓት በመበጀቱ የክልሉ ዜጎችን የዘመናዊ ዕውቀት ተቋዳሽ ማድረግ ተችሏል። በዚህ መሰረትም በ1987 ዓ.ም በክልሉ በነበሩ አጠቃላይ 189 የመጀመሪያና 4 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በከተሞች አካበቢ ተከፍተው በአንደኛ ደረጃ ለ39,123 ተማሪዎች እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ 1,087 በድምሩ ከ40 ሺ.ህ ለማይበልጡ ተማሪዎች ብቻ የመደበኛ ትምህርት አግልገሎት ይሰጡ ነበር።

ይህ ቁጥር በ2006 ዓ.ም በቅድመ መደበኛ ፣ በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ እና በጎልማሶች ጣቢያ በትምህርት ገበታ ላይ ያሉ ተማሪዎችና የጎልማሶች ቁጥር ከሰባት እጥፍ በላይ አድጎ ከ279,000 በላይ ደርሷል፡፡ የክልሉ መንግስትም ፍትሐዊ የትምህርት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ባለው ቁርጠኝነት መሰረት በተለይ ከ1997 ዓ.ም ወዲህ በየዓመቱ በአማካይ 25 የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እየገነባ ይገኛል። በከፍተኛ ትምህርት ረገድም በ1987 ዓ.ም በፊት በክልሉ ኮሌጅም ሆነ ዩኒቨርሲቲ ያልነበር ሲሆን በአሁኑ ወቅት ሶስት ኮሌጆች ( የመምህራን፣ የጤና እና የግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች) ፣ ሶስት የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች እና አንድ ዩነቨርሲቲ ተከፈተው

የትምህርትና የስልጠና አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪም ሁለት የአዳሪ ትምህርት ቤቶች ተከፍተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

ከ1987 ጀምሮ ከመደበኛው ትምህርት አገልግሎት ጎን ለጎን በአርሶ አደሩ አካባቢ አማራጭ የመሰረታዊ ትምህርት ስርዓት ተዘጋጅቶ የትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን በመክፈት ለዜጎች የትምህርት አግልገሎት መስጠት የተቻለ ሲሆን ከ1987 እስከ 2005 ዓ/ም ባለው ጊዜ የትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን ከ51 ወደ 202 በማሳደግ በየአመቱ በአማካይ ከ20 ሺህ በላይ ተማሪዎች ተጠቃሚ በማደረግ በዘርፉ መሰረታዊ ድል ማስመዝገብ ተችሏል።

የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት በማስፋፋት የትምህርትን ጥራትና ፍትሃዊነት ከማረጋገጥ አንጻር ሙሉ በሙሉ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጥባቸው 13 አዳዲስ ት/ቤቶች (4 በርትኛ፣ 5 ጉሙዝኛ፣ 3 ሺናሺኛ እና 2 በኮሞኛ) እንዲሁም የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንደ አንድ ትምህርት ዓይነት የሚሰጥባቸው 33 አዲስ ት/ቤቶች (17 በርትኛ፣ 11 ጉሙዝኛ፣ 5 ሺናሺኛ) በድምሩ 46 አዲስ ት/ቤቶችን በክልሉ የማስፋፋት ሥራ ተከናውኗል፡፡

የትምህርት ተደራሽነት፣ ጥራት፣ ብቃትና ፍትሃዊነት ለማሻሻል እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም ለማዳረስ የተነደፈውን የምዕተ ዓመቱን ግብ ለማሣካት አበረታች እንቅስቃሴ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሠረት የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች/1-8/ በ1983 ዓ/ም 189 የነበረው የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ቁጥር በ2006 ዓ/ም ወደ 536 አድጓል፡፡ የተማሪዎች ቁጥርም በ1987 ዓ/ም ከነበረው 39,123 በ2006ዓ/ም ወደ 194,978 አድጓል፡፡ ይህም የመማሪያ ክፍሎችን ቁጥር በ1987 ዓ/ም ከነበረበት ከ 830 በ2006 ዓ/ም ወደ 3,781 እንዲያድግ አስችሏል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የቅድመ መደበኛ ጥቅል ተሳትፎ ምጣኔ በ1987 ዓ/ም ከነበረበት 0 ፐርሰንት ወደ 32.8 በመቶ እና ከ1-8ኛ ክፍል ጥቅል ተሳትፎ በ1988 ዓ/ም ከነበረበት 47.6 በመቶ በ2006 ዓ/ም ወደ 114.6 በመቶ አድጓል፡፡ የአንደኛ ደረጃ ንጥር ተሣትፎ በ1988 ዓ/ም ከነበረበት 44.8 በመቶ በ2006 ዓ/ም ወደ 94 በመቶ አድጓል፡፡ በሴቶችና በወንዶች መካከል የነበረው የጥቅል ተሣትፎ ልዩነትም በ1988 ከነበረበት 40.7 በመቶ በ2006 ዓ/ም ወደ 22.6 በመቶ ጠቧል፡፡ በሌላ በኩል የሴቶችንና የነባር ብሄረሰቦች ከሌሎች ብሔረሰቦች አንፃር ድርሻውን ከፍ ለማድረግ በተደረገው ጥረት የሴቶችን ተሣትፎ /1-8/ በ1988 ከነበረበት 27 በመቶና የነባር ብሔረሰቦች ድርሻ በ1988 ከነበረበት 51.6 በመቶ አማራጭ ትምህርትን ጨምሮ ወደ 59.2 በመቶ ለማሣደግ ተችሏል፡፡

የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት በ1987 ዓ/ም ከነበረበት 4 በ2006 ዓ/ም ወደ 48( የግል ት/ቤት ጨምሮ) አድጓል፡፡ በ1988 ዓ.ም 4.9 በመቶ የነበረው የአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ /9-10/ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ በ2006 ዓ/ም ወደ 48.7 በመቶ አድጓል፡፡

የትምህርት ጥራትና ብቃት ከማረጋገጥ አኳያ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት /1-8/ የተማሪ መምህር ጥምርታ በ1987 37 ከነበረበት በ2006 ዓ/ም 39 የደረሰ ሲሆን በ2ኛ ደረጃ /9-12/ ደግሞ 24 ሆኗል፡፡ የተማሪ ክፍል ጥምርታ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት /1-8/ በ1987 ዓ/ም 47 የነበረው በ2006 ዓ/ም ወደ 49 እና በ2ኛ ደረጃ /9-12/ 68 የነበረው ወደ 59 ዝቅ ብሏል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ የክልሉ መንግስት የቀየሰው ዜጎችን ማዕከል ያደረገ የዕድገትና የልማት አቅጣጫ ምን ያህል ውጤታማና ስኬታማ እንደሆነ በግልፅ የሚያሳይ ነው።በትምህርት ዘርፍ በዋናነት ከሚታዩት ትግሮች መካከል የትምህርት ጥራት መጓደል እና የትምህርት ብክነት በመሆናቸው በቀጣይ ትኩረት አድርገን የምንሰራቸው ተግባሮቻችን ይሆናሉ፡፡

ሠንጠረዥ 12፡ የትምህርት ተሳትፎ

| ተ.ቁ | አመልካች | 1988 ዓ.ም | 2006 ዓ.ም | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የቅድመ መደበኛ ጥቅል ተሳትፎ በመቶኛ | - | 32.8 | |
| 2 | የአንደኛ ደረጃ (ከ1-8) ጥቅል ተሳትፎ በመቶኛ | 47.6 | 114.6 | |
| 3 | የአንደኛ ደረጃ ንጥር ተሳትፎ በመቶኛ | 44.8 | 94 | |
| 4 | የሥርዓተ ፆታ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ በመቶኛ | 40.7 | 22.6 | |
| 5 | የነባር ብሄረሰቦች የትምህርት ተሳትፎ በመቶኛ | 27 | 59.2 | |
| 6 | የሁለተኛ ደረጃ (ከ9-12) ጥቅል ተሳትፎ በመቶኛ | 4.9 | 48.7 | |

ምንጭ፡ የክልሉ ትምህርት ቢሮ

ሠንጠረዥ 13፡ የትምህርት ተቋማት ብዛት

| የትምህርት ተቋማት | 1987 ዓ/ም | 2006 ዓ/ም | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| አፀደ ህፃናት | 1 | 34 | 21 የግል አፀደ ህፃናት ት/ቤቶች |
| የመጀመሪያ ደረጃ (ከ1-8) | 189 | 536 | 10 የግል ት/ቤቶች |
| ሁለተኛ ደረጃ (ከ9-12) | 4 | 48 | 1 የግል ት/ቤት |
| ቴክኒክና ሙያ | - | 3 | |
| ኮሌጅ | - | 3 | |
| ዩኒቨርስቲ | 1 | 1 | |

ምንጭ፡ የክልሉ ትምህርት ቢሮ

ሠንጠረዥ 14፡ የመምህራን ብዛት (ምንጭ፡ የክልሉ ትምህርት ቢሮ)

| መምህራን | 1987 ዓ/ም | 2006 ዓ/ም | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| ቅደመ መደበኛ | - | 75 | |
| አንደኛ ደረጃ | 1,061 | 5,025 | |
| ሁለተኛ ደረጃ | 67 | 977 | |

ሠንጠረዥ 15፡ የመምህር ተማሪ ጥምርታ

| የትምህርት እርከን | 1987 | 2006 |
|---|---|---|
| አንደኛ ደረጃ (ከ1-8) | 1፡37 | 1፡39 |
| ሁለተኛ ደረጃ (ከ9-12) | 1፡57 | 1፡24 |

ምንጭ፡ የክልሉ ትምህርት ቢሮ

### 7.2 ጤና

ከደርግ ውድቀት በፊት በነበሩ ዘመናት ፍትሐዊ የሆነ የጤና ተደራሽነት ስርዓት ባለመኖሩ የክልላችን ህዝቦች በመከላከል ብቻ በቀላሉ ሊድኑ በሚችሉ በሽታዎች የተነሳ ለከፋ ችግር ሲጋለጡ ኖረዋል። በእነዚያን ዘመናት በክልሉ የነበሩ የጤና ተቋማት ብዛት እጅግ አነስተኛ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ያሉትም በዋና ዋና ወረዳ ከተሞቻችን ላይ ብቻ የታጠሩ በመሆናቸው ህዝቡ የእነዚህ ተቋማት ባለቤትና ተጠቃሚ አልነበረም። የተስተካከለ አደረጃጀት ያለመኖር፣ የሰለጠነ ባለሙያ እጥረት፣ የመድኃኒት አቅርቦት ችግሮች ተብትበው የያዟቸው ነበሩ።

ጤንነቱ በአግባቡ ያልተጠበቀና በተደጋጋሚ በበሽታ የሚጠቃ ዜጋ ምርትና ምርታማነት በመጨመር የራሱን ህይወት በቀጣይነት በማሻሻል የሀገር ቀጣይ ዕድገት ማረጋገጥ እንደማይችል ከጧቱ በትክክል የተገነዘበው የኢፌዴሪ መንግስት ህዝቡን ማዕከል ያደረገ እንዲሁም በመከላከል ላይ የተመሰረተ የጤና ልማት ፖሊሲ በማሰናዳት በቁርጠኝነት ተረባርቧል፡፡ በመሆኑም በክልላችን በ1983 ዓ.ም 2 ሆስፒታሎች፣ 3 ጤና ጣቢያዎች እንዲሁም 32 ክሊኒኮች ብቻ የነበሩ ሲሆን ልማታዊ መንግስታችን ለጤናው ዘርፍ በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት መሰረት ይህ ቁጥር በ2006 ዓ.ም ወደ 2 አጠቃላይ ሆስፒታሎች እና 4 የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙ ፣ 32 ጤና ጣቢያዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉና 8 በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙ ፣ 398 የጤና ኬላዎች አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ እና 22 በግንባታ ሂደት ላይ ናቸው፡፡

የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ሽፋኑም በ1983 ዓ.ም ከነበረበት 7 በመቶ በ2006 ዓ.ም ወደ 90 ከመቶ ከፍ ማድረግ ተችሏል።

በአሁኑ ወቅት 924 የጤና ኤክስቴንሽን ሙያተኞች በክልሉ በሚገኙ የከተማ እና የገጠር ቀበሌዎች ተመድበው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን በመፈፀም ላይ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ የክልላችን የእናቶችና ህፃናት ሞት በመቀነስ እንዲሁም የኤች አይቪ ኤዲስ ስርጭትን እንዲቀንስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ በወሊድ ምክንያት የሚሞቱ እናቶችና ህፃናት ሞትን ትርጉም ባለው መልኩ ከመቀነስ አኳያ ሁሉም ወረዳዎቻችን የአምቡላንስ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል።

በ2002 ዓ/ም ይፋ በሆነው የኢትዮጵያ ስነ-ህዝብና የጤና ዳሰሳ ጥናት መሠረት የክልሉ የእናቶች ሞት ቁጥር በ1992 ዓ/ም ከነበረበት 871 ወደ 676 ከ100,000 በህይወት ከሚወልዱት፣ ከአምስት ዓመት በታች ቁጥርም የህፃናት ሞት ቁጥርም በ1992 ዓ/ም ከነበረበት 198 ወደ 169 ከ1000 በህይወት ከሚወለዱት መወነሱ ተመልክቷል፡፡

የህፃናት ክትባት አገልግሎት ሽፋን በ1993 ከነበረበት 27 በመቶ በ2006 ዓ.ም ወደ 62.2 በመቶ፣ የቅድመ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ከ11 በመቶ ወደ 79 በመቶ፣ በሰለጠነ ባለሙያ የወሊድ አገልግሎት ከ4 በመቶ ወደ 18 በመቶ፣ የድህረ ወሊድ ክትትል አገልግሎት ከ1 በመቶ ወደ 33 በመቶ፣ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ከ5 በመቶ ወደ 43 በመቶ አድጓል፡፡

የወባ በሽታ ግንባር ቀደም የክልሉ ህዝብ የጤና ችግር ሆኖ የቆየ ቢሆንም በተካሄደው ዘርፈ-ብዙ የመከላከልና መቆጣጠር እንቅስቃሴ በተደረገው የቤተሰብ አልጋ አጐበር ሥርጭት የነፍሰጡር እናቶች እና ከአምስት ዓመት ህፃናት አጐበር ተጠቃሚነት በ1988 ከነበረበት 0 ፐርሰንት በ2006 ወደ 100 ፐርሰንት ያደገ ሲሆን በፀረ-ወባ ኬሚካል የተረጩ ቤቶች በ1988 ከነበረበት 33,883 ቤቶች በ2006 ወደ 169,300 ቤቶች ከፍ ብሏል፡፡ በሌላ በኩል የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ በሽታ ሥርጭት በ2002 ከነበረበት 2.2 በመቶ በ2006 ወደ 1.1 በመቶ ዝቅ ብሏል፡፡

ሠንጠረዥ 16፡ የጤና ሽፋን

| ተ.ቁ | አመልካች | 1983 ዓ.ም | 2006 ዓ.ም | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የጤና አገልግሎት ሽፋን በመቶኛ | 7 | 90 | |
| 2 | ከአምስት ዓመት በታች ያሉ ህፃናት ሞት ምጣኔ /ከ1000/ | 198(1992 ዓ/ም) | 169(2002 ዓ/ም) | |
| 3 | የእናቶች ሞት ምጣኔ /ከ100,000/ | 871(1992 ዓ/ም በአገር ደረጃ) | 676(1992 ዓ/ም በአገር ደረጃ) | |
| 4 | የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተጠቃሚዎች በመቶኛ | 5 | 43 | |
| 5 | በሰለጠነ የጤና ባለሙያ የታገዙ ወላዶች ብዛት በመቶኛ | 4 | 18 | |
| 6 | በወባ መከላከያ አጎበር ተጠቃሚ የሆኑ የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች በመቶኛ | - | 100 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 7 | የኤች.አይቪ/ኤድስ ሥርጭት በመቶኛ | 2.2(በ2002 ዓ/ም) | 1.1 | |

ምንጭ፡ የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ

ሠንጠረዥ 17፡ የጤና ተቋማት ብዛት

| የጤና ተቋማት | 1983 ዓ/ም | 2006 ዓ/ም | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| ጤና ኬላ | 32 | 398 | |
| ጤና ጣቢያ | 3 | 40 | 8 ጤና ጣቢያዎች ግንባታቸው በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡ |
| የመጀመሪያ ሆስፒታል | - | 4 | 4ቱም ሆስፒታሎች በግንባታ ላይ ናቸው፡፡ |
| አጠቃላይ ሆስፒታል | 2 | 2 | |
| የግል ክሊኒክና ፋርማሲ | - | 249 | |

ምንጭ፡ የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ

ሠንጠረዥ 18፡ የጤና ባለሙያ ብዛት

| ጤና ባለሙያ | 1983 ዓ/ም | 2006 ዓ/ም |
|---|---|---|
| ስፔሻሊስት ሀኪም | - | 1 |
| ጠቅላላ ሀኪም | 1 | 19 |
| ጤና መኮነን | - | 107 |
| ነርስ | 6 | 897 |
| ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ | - | 924 |

ምንጭ፡ የክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ

## ክፍል ስምንት፡- የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች

በክልላችን ባለፉት 23 አመታት ያስመዘገብነው የኢኮኖሚ እድገት እጅግ የሚያበረታታ ነው፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተቀርፆ በክልላችንም በመተግበር ላይ የሚገኘው ፖሊሲ የምዕተ አመቱን የልማት ግቦች ለማሳካትም ይሁን በክልላችን ተንሰራፍቶ የሚገኘውን ድህነት ለመቅረፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ ለትግበራው ሁላችንም መረባረብ የሚገባን ይሆናል፡፡

ያም ሆኖ የእስካሁኑ ስኬታችን ለቀጣይ ስራ ይበልጥ መነሳሳትን ይፈጥርልናል ወይም በትልቁ እያቀድን ለትላልቅ ስራዎች ያነሳሳናል እንጂ በድላችን ተኩራርተን የሚያዘናጋን አይደለም፡፡ አሁንም ዋናው ጠላታችን ድህነት በመሆኑ እሱን ከመታገል ለአፍታም ቢሆን መዘናጋት የለብንም፡፡

የተገኘው የኢኮኖሚ እድገት የህብረተሰቡ ኑሮን በማሻሻሉ ድህነት እየቀነሰ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ልማታችን ይበልጥ በማፋጠን እጅ ለእጅ ተያይዘን ከድህነት ጋር የምናደርገውን ትግል በአሸናፊነት መደምደም ይኖርብናል፡፡

በቀጣይ የሚጠበቀው የኢኮኖሚ እድገት ስሌት የሚመሠረተው ባለፉት ዓመታት በተገኘው ከፍተኛ እድገት ላይ በመሆኑ እስካሁን የተመዘገበውን የኢኮኖሚ እድገት ቀጣይነት ማረጋገጥ እንዳለ ሆኖ ተጨማሪ እድገት ማስመዝገብ ፈታኝ መሆኑ አጠያያቂ አይሆንም፡፡ ስለዚህ የኢኮኖሚውን ቀጣይነት ለማረጋገጥ በሁሉም ዘርፎች የልማት ኃይሎችን በማቀናጀት ርብርብ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ ለዚህ ደግሞ በተለያዩ መስኮች ጀምረነው መልካም ውጤቶችን ያስመዘገብንበትን የልማትና የለውጥ ሰራዊት ግንባታ እንደ ቁልፍ የስኬቶቻችን ማበልፀጊያና የችግሮቻችን መፍቻ መሳሪያ ልንጠቀምበት ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የቃል ኪዳን ሰነድ የሆነው ህገ መንግሰታችን እንዲፀድቅ ሆኗል፡፡ ህገ መንግስቱን በማርቀቅም ሆነ በማፅደቅ ሂደት ውስጥ ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች በስፋት እንዲመክሩበትና እንዲወከሉበት ተደርጓል፡፡ ህገ መንግስቱ ለዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተለይም ለቡድንና ለግል መብቶች እውቅና በመስጠት ለህዝባችን የዘመናት የፖለቲካ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል፡፡

ህገ መንግስቱን መሰረት በማድረግም በአገራችን ብሎም በክልላችን ታሪክ ባልነበረ መልኩ ነፃ፣ ፍትሃዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ወቅታቸውን የጠበቁ ምርጫዎችንም አካሂደናል፡፡ በእያንዳንዳቸው ምርጫዎችም ለቀጣዮቹ ምርጫዎች ስኬታማነት የሚያግዙ ልምዶችን ወስደናል፡፡ ህብረተሰቡም ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን የመጠየቅና የመጠቀም ግንዛቤው እያደገ በመሄዱ የምርጫ ተሳትፎው እየጨመረ ሄዷል፡፡

ለዴሞክራሲ መሰረት የሚሆኑ ተቋማትን ባለፉት አመታት ገንብተናል፡፡ ህገ መንግስታዊ ተልዕኳቸውን በብቃት እንዲወጡ ለማድረግ ግን የተቋሞቹን ውስጣዊ አቅም በማጠናከር ዲሞክራሲያችንን በማይናወጥ መሰረት ላይ መገንባት ያስፈልገናል፡፡ በሁሉም የትምህርት ተቋሞቻችን፣ ሲቪል ሰርቪስና የመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ህገ መንግስቱን የማስረፅ በተለይም የህግ የበላይነትንና የህዝብ የስልጣን ባለቤትነት በመሳሰሉት አጀንዳዎች ላይ ትኩረት ሰጥተን መረባረብ አለብን፡፡

ሌላው ትኩረት ሰጥተን ልንፈፅመው የሚገባን መልካም አስተዳደርን በየደረጃው የማስፈን ጉዳይ ነው፡፡ የክልላችን ህገ መንግስት አገልግሎት አሰጣጣችን ግልፀኝነትና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን ይደነግጋል፡፡ ሆኖም በአገልግሎት አሰጣጣችን ዙሪያ አሁንም ያልተፈቱ በርካታ ችግሮች አሉ፡፡ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፓኬጆችንና የለውጥ ሪፎርሞችን በመቅረፅ በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች የአገልግሎት አሰጣጣችንንና የህዝቡን የልማት ጥያቄዎች የመመለስ አቅማችንን ለማሳደግ በለውጥ ሰራዊት መልኩ ተንቀሳቅሰናል፡፡ የተገኘው ውጤትም አበረታች ነው፡፡ በርግጥም ያለ መልካም አስተዳደርና የህዝብ ተሳትፎ የዚህ አይነት ፈጣን ሀገራዊና ክልላዊ እድገት ማስመዝገብ የሚቻል አልነበረም፡፡ ይሁንና በመልካም አስተዳደር ረገድ የምንመዘነው ባስገኘነው የህዝብ /ተገልጋይ/ ርካታ መጠን እንደመሆኑ ከሰራነው ይልቅ ወደፊት የሚጠብቀን ስራ ይበዛል፡፡

ህብረተሰቡ ቅሬታ ከሚያቀርብባቸው ጉዳዮች ውስጥ አሁን ባለን አቅምና አደረጃጀት በቀላሉ የሚፈቱ አሉ፡፡ እነዚህን በህዝብ /ተገልጋይ/ መድረኮቻችንና በለውጥ ሰራዊት አደረጃጀቶቻችን አማካኝነት ነቅሰን በመለየት ፈጣን ምላሽ መስጠት ይጠበቅብናል፡፡ አገራዊና ክልላዊ እድገታችንና ልማቱ

የፈጠራቸው ነገር ግን አሁን ባለን አቅም ልንፈታቸው የማንችላቸውን የህዝቡን የልማት ጥያቄዎች ደግሞ በጋራ በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫዎችን አብረን መቀየስ፣ በአተገባበራቸውና ቅደም ተከተላቸው ላይም ከህዝቡ ጋር መግባባት ላይ መድረስና በተግባባንበት ልክ ለመፈፀምም በፅናት መረባረብ አለብን፡፡

የልማትም ሆነ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታችን ተጠናክሮ የሚቀጥለው በክልላችን የሰፈነው ሰላም መቀጠል ሲችል ብቻ ነው፡፡ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በክልላችን በመገኘቱ እና ሰላም የናፈቀው የደቡብ-ምስራቅ ሱዳን አዋሳኝ በመሆናችን የክልላችንን ሰላምና እድገት የማይፈልጉ አንዳንድ የውጭና የውስጥ ሃይሎች የጥፋት አጀንዳቸውን በመቅረፅ ሊያተራምሱን መሞከራቸው አልቀረም፡፡ ለረጂም ጊዜ ያክል ሰላም ሰፍኖበት የቆየውን ክልላችንን የሚፈታተን አንዳንድ ድርጊቶች እያዬን ያለን በመሆኑ ክልላችንን ብሎም የህዳሴ ግድባችንን በንቃት መከታተልና መጠበቅ የዜግነት ግደታችን ጭምር ነው፡፡

በሃይማኖት ሽፋን አክራሪነትን ለማስፋፋት ጥረት የሚያደርጉ ሀይሎችም አሉ፡፡ የአክራሪነት አደጋው በህዝብና በመንግስት የጋራ ጥረት እየተመከተ ያለ ቢሆንም ግዜውን ጠብቆ ብቅ ማለቱ ስለማይቀር ከልማት ስራችን ጎን ለጎን ልንታገለው ይገባል፡፡

የሃይማኖት አክራሪነት ግቡ ሃይማኖታዊ አይደለም፡፡ ይልቁንም የተወሰኑ ሃይሎች በዴሞክራሲያዊ መንገድ ማሳካት ያልቻሉትን ፍላጎታቸውን በሃይማኖት ሽፋን በሃይል ለመጫን የሚጠቀሙበት ስልት ነው፡፡ በተለያዩ ሀገራት በግልፅ እንደሚታየውና በእኛ ሀገርም እንደተከሰተው የሃይማኖት አክራሪነት ከሽብርተኝነት ጋር ቀጥተኛ ትስስር ያለውና የውጭ ሃይሎች እጅ ጣልቃ የሚገባበት ነው፡፡ ስለሆነም በፀረ ድህነት ትግላችን ላይ የተጋረጠ አደጋ መሆኑን ተገንዝበን አምርረን ልንታገለው ይገባል፡፡

በአገራችን የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብት አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ተከብሮ በዴሞክራሲያዊ አንድነት አዲሲቷን ኢትዮጵያን የመገንባት የ23 አመት የተሳካ ጎዞ ተጉዘናል፡፡ ብዝሃነትን በአግባቡ ያስተናገደው የፌደራል ስርአታችን ከእኛ አልፎ የሌሎችን ቀልብ መሳብ ጀምሯል፡፡ ይህ በጠንካራ መሰረት ላይ እየገነባነው የምንገኘው ዴሞክራሲያዊ አንድነት የእግር እሳት የሆነባቸው የውጭና የውስጥ ሃይሎች በብሄር ብሄረሰቦች መካከል ቅራኔና ግጭት ለመፍጠር የተለመደ በሬ ወለደ ቅጥፈታቸውን ተያይዘውታል፡፡ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ስለሆነም ይህንን መሰሪ ድርጊታቸውን በመታገልና በማክሸፍ ለቀጣይ ስኬት መረባረብ ይኖርብናል፡፡

በአጠቃላይ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የህዳሴ መሰረት የሆነውንና የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሉዓላዊነት መገለጫ የሆነውን ሕገ መንግስታችንን እንደ ዓይናችን ብሌን በመጠበቅ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደታችንንና መልካም አስተዳደርን የማስፈን ትግላችንን አጠናክረን በማስቀጠል ከፊጣኑ የኢኮኖሚ ዕድገታችን በተጣጣመ መልኩ ለማስኬድ የላቀ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል።

## ማጣቀሻዎች

Abebe Ano.(2010). *The Shinasha of Metekel: North-western Ethiopia: a Historical Survey to 1974*; MA. Thesis, Department of History, School of Graduate Studies, Adama, Adama University.

አቦሽ ሙስጠፋ፡፡ (2004 ዓ/ም)፡፡ስርዓተ አምልኮና ሌሎች ባህላዊ ክንዋኔዎች በማኦና ኮሞ ብሔረሰቦች፡፡ አሶሳ፣

አዲሱ አዳሜ፡፡ (1992 ዓ/ም) ፡፡ የሺናሻ ባህልና ታሪክ፡፡ ቡለን፣(ያልታተመ)፡፡

አዲስ ምዕራፍ፣10ኛ ዓመት፣ቁ.12 ፣ አሶሳ፣ 2006

አልከድር አህመድ ሳይድ፡፡ (2006 ዓ/ም)፡፡ አሶሳ፣ (ያልታተመ)፡፡

ዓለሜ እሸቴ፡፡ (1967 ዓ/ም) :: የኢትዮጵያ ህዝብ ወሰንና እንዲሁም ክፍላተ ሀገራት አስተዳደር በታሪክ 1800-1813፡፡

Alessandro Triulzi.(1981). *Salt Gold Legitimacy Prelidi to the History of No Man Land Belashangul,Welega* Ethiopia/ca,1800-1898.

አጠይብ አህመድ፡፡ (1973)፡፡ የበርታ ታሪክና ባህል፡፡ ከተለያዩ ጽሁፎቻቸው የተወሰደ፡፡

Bahru Zewde. (2004). *Modern History of Ethiopia 1855-1974*, Addis Ababa, Addis Ababa University Press.

በቀለ ወ/ማሪም፡፡ (1996 ዓ/ም)፡፡ "የካፋ ሕዝቦች እና መንግስት አጭር ታሪክ"፡፡ አዲስ አበባ፡ ሜጋ ማተሚያ ቤት፡፡

Bender, Leonel. (1981). *People and Cultures of the Ethio-Sudan Borderlands, East Lansing*: Michigan University.

Bender, Marvin Lionel. (1969). *Distribution and Classification of Ethiopian Language, Cushitic and Gongä. In Fleming, H.C. and Bender, M.L. Language Survey of Ethiopia* (Mimeographed*)*, Addis Ababa.

Crosby, Oscar. (1901). "*Notes on a Journey from Zeila to Khartoum," In: The Geographical Journal. Including the Proceedings of the Royal Geographical Society*, London, XVIII, 46-61.

Debella Alemu. (2000). *History of Däbrä-Zäyt Town from its Foundation to 1991: Wänbära*, B.A. Thesis Submitted to Department of History A.A.U.

Ethiopian Central Statistical Authority. (2007). *Report on Population and Housing Result*, a First Draft, Addis Ababa.

ፊቃዱ ደሳለኝ፡፡ (1993 ዓ/ም)፡፡ የበርታ ብሔረሰብ ታሪክና አኗኗር፡፡ ሆሣ፣ቁ.4፣ት/ቤት፡፡

Fleming Harold. (1976). "*Käfa (Gongä) Languages," Marvin Lionel Bender (ed.), The Non-Semitic Languages of Ethiopia*, Michigan, 351-376.

Lange, Warner J. (1982). *History of the Southern Gongä (South-Western Ethiopia)*, Wiesbaden.

Lionel Bender, Marvin. (1969). *Distribution and Classification of Ethiopian language, Cushitic and Gongä, In: Fleming, H.C. and Bender, M.L. Language Survey of Ethiopia* (Mimeographed), Addis Ababa.

Ralf Sibert, Klaus and Charlotte Wekind. (2002). SIL, International.

ሽብሩ ድባና ምትኩ መኮርያ፡፡ (1994 ዓ/ም)፡፡የማኦ ብሂረሰብ አኗኗር ፤ወግና ባህሎች ታርካዊ ጥናት፡፡ ዲባጤ ከ/ሁ/ደ/ት/ቤት፡፡

Third S.L.L.E. Servey on Languges of the Begi/Assosa Area

Taddase Tamarat. (1988). "*Nilo-Saharan Interactions With neighbouring highlanders," The case of Gumuz of Goǧǧam and Wallagga. In the Proceedings of the workshop on Famine of Experience and Resettlement in Ethiopia*, 1988a, 7-12.

TARESSA QANNO CHAKA.( 2011). SCHOOL OF MISSION AND THEOLOGY.

Tessema Ta'a. (1980). "*The Oromo of Wallagga: A Historical Survey to 1910",* M.A.Thesis, Department of History, Addis Ababa University School of Graduate Studies

TESFAYE ZERGAW AYANU,YASIN MOHAMMED.RUFFO/A.M/1995/2002.

Tsega Endalew. (1997). "*The Oromo of Wänbära: A Historical Survey to 1941."* M.A. Thesis in History, Addis Ababa University School of Graduate Studies.

የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን፣ አዲስ አበባ፣ 2003

ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል፣ዶክሜንተሪ ፊልም፣ አዲስ አበባ፣1996

Wandy James.(1979). *Lifelines Exchange Marriage among Gumuz*/148-175/. Oxford University.

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድና የለውጥ ጉዞአችን፡ ለመከከለኛ አመራር ስልጠና የተዘጋጀ ሠነድ፣ አሶሳ፣ መጋቢት 2004

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት መስተዳደር ምክር ቤት የ2006 በጀት ዓመት የሥራ ክንውን ሪፖርት፣ አሶሳ፣ ሐምሌ 2006

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የተመዘገቡ ውጤቶች ሪፖርት፣ አሶሳ፣ ሐምሌ 2006

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ባላፉት 23 ዓመታት በክልሉ የተመዘገቡ ውጤቶችና ለውጦች የሚገልፅ ሪፖርት፣ አሶሳ፣ ሰኔ 2006

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በላፉት 23 ዓመታት በትምህርት ዘርፍ የተመዘገቡ ውጤቶች ሪፖርት፣ አሶሳ፣ ሰኔ 2006

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በላፉት 23 ዓመታት በትምህርት ዘርፍ የተመዘገቡ ውጤቶች ሪፖርት፣ አሶሳ፣ ሰኔ 2006

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የምግብ ዋስትና ሕዝብ አሠፋፈር አደጋ መከላከል ዝግጁነት ጽ/ቤት የመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራም ሪፖርት፣ አሶሳ፣ ሰኔ 2006

የቤንሻንጉል ጉሙዝ መስተዳድር ም/ቤት፣ የክልል፣የተወካዮች ም/ቤት፣የ ወረዳና የቀበሌ ም/ቤት አባላት ዝርዝር ሪፖርት፣ አሶሳ፣ ሐምሌ 2006

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በላፉት 23 ዓመታት በዘርፍ የተመዘገቡ ውጤቶችና ለውጦች ሪፖርት፣ አሶሳ፣ ሐምሌ 2006

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ገጠር መንገዶች ባለስልጣን የመንገድ መሠረተ ልማት ንፅፅር ሪፖርት፣ አሶሳ፣ ሰኔ 2006

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት፣ አሶሳ፣ ነሀሴ 2006

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ የሥራ ሪፖርት፣ አሶሳ፣ ሰኔ 2006

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የውሃ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ በላፉት 23 ዓመታት በዘርፍ የተመዘገቡ ውጤቶች ሪፖርት፣ አሶሳ፣ ሐምሌ 2006

ህገ መንግስት ትሩፋቶች 7ኛው የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በዓል አከባበር ሲምፖዚየም፡ በኢፌዲሪ የፌዴሬሽን ም/ቤትና በባህርዳር ዩኒቨርስቲ የተዘጋጀ ፕሮሲዲንግ ባህርዳር፣ መስከረም 2006